# በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ላይ የተዘጋጀ ስልጠና

በማርቆስ በቀለ

ከጥቅምት 02 – 04 ቀን 2006 ዓ.ም

ደብረ ማርቆስ

# የቅጣት አወሳሰን  መሠረታዊ መርሆዎች በኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ

## 1. የህጉን ዓላማና መንፈስ መከተል

- በወንጀል ህግ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቷቸው ከሚቀረፁ ድንጋጌዎች መካከል ዓላማና ግቦች ይገኙበታል፡፡
- በአንድ ህግ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለፁ ዓላማና ግቦች ህጉ የቆመበትን ምክንያትና የሚታሰበውን ውጤት ጠቅለል አድርገው የሚያመለክቱ ናቸው፡፡
- የወንጀል ህግ የአንድን ህብረተሰብ እሴቶች (values) የሚያንፀባርቅና የሚያራምድ የህብረተሰብ መሣሪያ ነው፡፡
- እነዚህ እሴቶች ሕሊናዊ /ሞራላዊ/፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
    - የህሊና እሴቶች የትክክልና ስህተት መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
    - ኢኮኖሚያዊ እሴቶች ደግሞ ንብረት ማፍራትን፣ በንብረት መጠቀምንና የሀብት ክፍፍልን ወይም ስርጭትን የሚመለከቱ ሲሆን
    - የፖለቲካ እሴቶች በበኩላቸው በግለሰቦችና በመንግስት መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት የሚመለከቱ ናቸው፡፡

# Contin…..

- በመሆኑም ስለተጠቀሱት እሴቶች ዝርዝር ይዘትና የጥበቃ ደረጃ እያንዳንዱን ድንጋጌ በማዬት መገንዘብ ይቻላል፡፡
- ወንጀል ማህበራዊ ክስተት እንደመሆኑ መጠን በማናቸዉም ጊዜ ህጉ ያስቀመጠውን ማስጠንቀቂያ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ሊፈፀም ይችላል፤ ይህ በሆነ ጊዜ ቅጣት የማይቀር ሆኖ ይመጣል፡፡
- ስለዚህ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ውስጥ ቅጣት ግብ ሣይሆን የወንጀል መከላከሉን ግብ ለማሣካት የተቀመጠ አንዱ ስልት ነው፡፡
- የወንጀል ህግ ሕብረተሰብን ከጉዳት ለመጠበቅ ሲባል የሚወጣና እንደወንጀል የሚቆጠሩ ድርጊቶችንና ለእነዚህ ድርጊቶች ተገቢ የሆኑ ቅጣቶች ተዘርዝረው የሚገለፁበት ህግ ነው፡፡
- በሕጉ ውስጥ ተዘርዝረው የሚገኙት የወንጀል ዓይነቶች ቢፈፀሙ ወይም ቢሞከሩ ሕብረተሰቡን የሚጐዱ ስለሆኑ እንዲሁም ሕብረተሰብ በሕብረተሰብነት እንዲቀጥል ራሱን ከጉዳት መጠበቅ ስላለበት የወንጀል ህግን አንድ መሣሪያው አድርጐ ይጠቀምበታል፡፡

- የወንጀል ህግ የሕብረተሰብን ሰላምና ደህንነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በየጊዜው የሚኖሩ ለውጦችን ለማስቀጠል የሚያግዝ ቁልፍ መሣሪያ ነው።
- በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያቶች ወጥተው የነበሩ የወንጀል ህጎችን ስንዳስስ አንዱ በሌላው ለመተካት በምክንያትነትን የተጠቀሱትን ማህበራዊ፣ ኢካኖሚያዊና ፖለቲካዊ እውነታቸው ተንፀባርቀው እናገኛለን።
- በ1949 ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥራ ላይ ከዋለ ወደ ግማሽ ምዕተ ዓመት የተጠጋው በመሆኑ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሥር ነቀል የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች የተካሄዱ በመሆኑና ከዚህ ሁሉ ለውጥ በኋላ እንዲቀጥል ማድረግ አግባብነት እንደማይኖረው ተገልጿል።
- በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ ከአሁኑ በፊት ወንጀል ናቸው ተብለው ያልተለዩ ጉዳዮች ወንጀል ሆነው የሚደነገጉበት ወይም በወቅቱ በነበረው የማህበረሰቡ ሁኔታ ያስቀጡ የነበሩ ጉዳዮች ወንጀል መሆናቸው ቀሪ የተደረጉበትን ሁኔታ እንመለከታለን።
- በእርግጥ ጐጅነታቸው በሣይንስ የተረጋገጠውን ልማዳዊ ድርጊቶችን መፈፀም ያስቀጣል በማለት በህግ መደንገግ የሚቻል ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ የህብረተሰቡን ይሁንታ ማግኘት አዳጋች እንደሚሆን የታወቀ ነው።

- ለ1949 የወንጀለኛ ህግ መቅጫ መለወጥ በምክንያትነት የተነሱ መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህን ምክንያቶች መረዳት በህገራችን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የተካሄዱ ለውጦችን ለመገንዘብ ያግዛል፡፡
- ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ሕግ አውጭው ዘመናዊ ህግ በማውጣት ህብረተሰቡን በማስተማርና በመምራት ከጐጂ ባህሎች እራሱን እንዲያላቅቅ ማድረግ እንደሚገባው በወንጀል ህግ ፍልስፍና የሚደገፍ ነው፡፡
- የወንጀል ህግ የህብረተሰብ ለውጥ መሣሪያ ነው የሚባለውም በነዚህና በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች ናቸው፡፡
- ከላይ እንደተገለፀዉ አንድ ህግ ሲወጣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈታው ችግር ይኖራል፤ ህጉ የሚፈፀመዉም የተቀመጠውን ዓላማ ለማሣካት ነው፡፡
- ነገር ግን አፈፃፀሙ ከህጉ ዓላማ በተቃራኒ የሚሄድ ከሆነ አለ የተባለውን ችግር መፍታት ቀርቶ ህጉ ራሱ ሌላ ችግር ይሆናል፡፡
  - ➢ ለምሣሌ የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ ዓላማ ሰላምና ደህንነት መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሣካት ከተቀመጡ ስልቶች መካከል አንዱ በአጥፊዎች ላይ ተገቢውን ቅጣት መወሰን ነው፡፡

# Contini.....

- ቅጣቶችና የጥንቃቄ ርምጃዎች የሚወሰዱት ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማሳካት ሲሆን አፈፃፀማቸውም የህጉን መንፈስ (sprit) መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡
- ህግ ሊፈፀም የሚገባው ዓላማዉን ለማሣካት በሚያስችል መልኩ መሆን አለበት የሚለው ሃሳብ በብዙ መልኩ ሊያስማማ የሚችል ቢሆንም አፈፃፀሙም በዚሁ መሠረት ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ሊያስቸግር ይችላል፡፡
- በእርግጥ የአንድን ህግ ዓላማ ከተወሰኑ ድንጋጌዎች ብቻ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡
- በአጠቃላይ የህጉን ዓላማና መንፈስ የተከተለ ቅጣት መወሰን አንዱ የቅጣት አወሳሰንን መርህ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

# ¡d¸E

2. <u>የአጥፊውን የግል ሁኔታ፣ የወንጀሉን ከባድነትና አፈፃፀም መሠረት ያደረገ ቅጣት</u>

- ይህንን መርህ በተመለከተ የተለያዩ አስተሣሰቦች ይራመዳሉ፡፡
- በተለይ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀሉን ከባድነት በማዬት፣ የወንጀል አድራጊውን ዓላማ ሁኔታዎች በማመዛዘን፣ የወንጀሉን ከባድነት ለብቻ በመመዘን ወይስ የተጠቀሱትን በሙሉ በአንድነት በማገናዘብ የሚለው ምላሽ የሚያስፈልገው ነው፡፡
- ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽም የአንድ አገር የቅጣት ዓላማ ትኩረት ምን እንደሆነ ፍንጭ ሊሰጥ የሚችል ነው፡፡
- ቅጣት የወንጀሉን ከባድነት ብቻ መሠረት በማድረግ መወሰን የሚለዉን አስተሳሰብ የምንቀበል ከሆነ የወንጀል ፈፃሚው ያለፈ የህይወት ታሪክ፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የሃሳቡ ዓላማ፣ የግል ኑሮው ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃው ወዘተ…ዋጋ አይሰጣቸውም፡፡
- በዚህ መሰረት የሚወሰን ቅጣት ውጤቱ ብቀላ ከመሆን አያልፍም፡፡

- በሌላ በኩል የወንጀሉን አደገኛነት ወይም የአፈፃፀሙን ሁኔታ ወደ ጐን በመተው የወንጀል ፈፃሚውን የግል ሁኔታዎች ብቻ በመመልከት መወሰን ያልተገባ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡
- በመሆኑም የተሻለ አማራጭ ሆኖ የሚታየው ሁሉንም በመመዘን መወሰን ነው፡፡
- የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ መሠረታዊ መርህ አድርጐ የተነሣውም
  - በአንድ በኩል የአጥፊውን የግል ሁኔታዎች
  - በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀሉን ከባድነትና አፈፃፀም በመመዘን ቅጣቱን መወሰን ነው፡፡
- ስለዚህ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ መሠረት ቅጣት ሊወሰን የሚገባው
  - የወንጀል አድራጊውን የአደገኝነት መጠንና ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣
  - ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የአሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣
  - የትምህርቱን ደረጃ
  - እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በመመዘን ነው፡፡
- እነዚህ ሁኔታዎች እንደነገሩ ሁኔታ ቅጣትን ለማክበድ ወይም ለማቅለል ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው፡፡

3. <u>ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በመመርመር መወሰን</u>

- የሀገራችንን የቅጣት አመዳደብ ስርዓት ስንመለከት ህግ አውጭው ለአንድ የወንጀል ድርጊት ያስቀመጠው መነሻ እና ጣሪያ አለ።
- የህጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቶች እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ተገቢ የሆነውን ቅጣት መወሰን አለባቸዉ።
- ይህንን ድንጋጌ አስመልክቶ ህግ አውጭው ባደረገው ውይይት፡-
  - ዳኞች በተሻለ መጠን ከዝቅተኛው ቅጣት መጀመር እንዳለባቸው፣
  - ሰዎችን በእስራት በመቅጣት እስረኛን ከማብዛት ይልቅ አማራጭ ቅጣቶችን አስቀድሞ መመርመር እንደሚገባ እና
  - በአጠቃላይ ይህ ድንጋጌ በወንጀል ህጉ ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣል ተብሎ እንደተገመተ ገልጿል።
- ይህ ግምት በእርግጥም በተግባር እየተፈፀመ ነው ወይ? የሚለው የበለጠ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም ቢያንስ በመርህ ደረጃ መከተቱ አስፈላጊ ነዉ ።

# continti

- ድንጋጌው “በልዩ ህጉ ክፍል የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው” የሚል ሀረግ ይዟል።
- አንዳንድ ጊዜ ህግ አውጭው ግልፅ የሆነ መነሻ ቅጣት ቢያስቀምጥም ፍ/ቤቶች በህግ መሠረት ከመነሻ ቅጣቱ ወርደው መወሰን ይችላሉ።
- ነገር ግን እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ከሌሉ ቅጣቱን የሚወስኑት ህግ አውጭው ለድንጋጌው ባስቀመጠው መነሻና መድረሻ ውስጥ መሆን አለበት።
- ስለዚህ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛ ቢባልም ገደብ ያለው መሆኑን ለመጠቆም የገባ ሀረግ ነው።
- ይህ መርህ ወደ ከባዱ ቅጣት ለመድረስም የሚያገለግል ነው።
- አንድ ወንጀል አድራጊ ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ የተቀመጠውን ከፍተኛ ቅጣት ወይም ልዩ ማክበጃ ምክንያቶች ካሉ ደግሞ ጠቅላላ ክፍሉ ለወንጀሉ ዓይነት የመጨረሻ ቅጣት ብሎ እስከወሰነው ድረስ ሊቀጣ ይችላል።

## 4. ለቅጣት አወሳሰን የሚረዱ የህጋዊነት መርሆዎችን መከተል

- የወንጀል ህግ የሚመራባቸው መሠረታዊ መርሆዎች መኖራቸዉ ይታወቃል። ለምሳሌ ማንም ሰው በህግ መሠረት የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ከዚህ ቀደም በተቀጣበት ወይም ሌላ ህጋዊ ርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና ሊከሰስ ወይም ሊቀጣ እንደማይችል ህገ-መንግስቱን ጨምሮ በበርካታ የሰብአዊ መብት ሰነዶች ተገልጿል።
- ይህ የህጋዊነት መርህ ለህግ ባለሙያዎች አዲስ ባይሆንም በስራ ሂደት ይህንን መርህ የሚጥሱ ውሣኔዎች መታዬታቸው አልቀረም።
- ይህንን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ እስከ ፌዴራል ሰበር ድረስ ክርክር ተካሂዶበት እልባት ያገኘን አንድ መዝገብ እናነሣለን።

- አንድ ሰው የወንጀል ህጉን አንቀፅ 556 ንዑስ አንቀፅ 2(ሀ) በመተላለፍ የድብደባ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ከተከሰሰ በኋላ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ይቀጣል።
- ድብዳባ የተፈፀመባቸዉ ግለሰብም ከጊዜ በኋላ የሞቱ ሲሆን የሞታቸው ምክንያት ድብደባው ስለመሆኑ በሆስፒታል ማስረጃ ይረጋገጣል።
- ይህንን መሠረት በማድረግ ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህጉን አንቀፅ 540 በመጥቀስ ግለሰቡ የግድያ ወንጀል ፈፅሟል በማለት አዲስ ክስ ይመሰርታል።
- ተከሣሽ በድጋሜ ልቀጣ አይገባኝም ብሎ ቢከራከርም  የስር ፍርድ ቤቱ የአስር አመት ፅኑ እስራት ወሰነበት። ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ ባለበት አፅንቶታል።

- ጉዳዩ በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ይግባኝ የቀረበላቸው የክልልና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎቶች በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 23 እና የወንጀል ህጉን አንቀፅ 2(5) የጣሰ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ተከሣሽ በነፃ እንዲሰናበት ወስነዋል፡፡
- ይህ ዉሳኔ በእርግጥም ተገቢ ነዉ፤ ምክንያቱም፡-
  - በመጀመሪያ ደረጃ ዐቃቤ ህግ ክስ ከመመስረቱ በፊት ይህንን አለማገናዘቡ አንድ ስህተት ሲሆን
  - የወረዳና ከፍተኛ ፍ/ቤቶችም በመቀበል ቅጣት መወሰናቸው በእርግጥም መሠረታዊ የህግ ስትተት ነው፡፡
- ስለዚህ የህጋዊነት መርሆዎችን መመርመር አስፈላጊ ነዉ፡፡

## 5. የአወሳሰንን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነትን ማረጋገጥ

- የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አዉጥተዉ በተገበሩ አገሮች እንዲሁም ስለቅጣት አወሳሰን በተጻፉ የምርምርና የጥናት ጽሁፎች ከቅጣት አወሳሰን ጋር በተያያዘ የቅጣት አወሳሰን ሊገዛባቸው የሚገቡ መርሆዎችን ያስቀምጣሉ።
- እነዚህም በአጭሩ የሚከተሉት ናቸው።
  - ተመዛዛኝነት/proportionality/፡- ይህ መርህ ከተከሰሰዉ ሰዉ አንፃር የሚታዩ ሆኖ የቅጣት ዉሳኔዉ ሊሰነዝር የሚገባዉ ዉስን የሆኑ ነገሮችን በመንተራስ ሳይሆን የወንጀሉን ዓይነት፣ ክብደት፣ የተከሳሹን የጥፋተኛነት ደረጃ እና ያለፈ የወንጀል ታሪኩን በማገናዘብ መሆን እንዳለበት ነዉ።
  - ወጥነት/consistency/፡-
    - በእርግጥ ወንጀል ግላዊ ባህሪ ያለዉ በመሆኑ የአንዱ ምክንያት ለሌላዉ የሚተላለፍ አይደለም።
    - ይህ ማለት ግን ወጥ በሆነ መልክ ተመሳሳይ የሆኑ የወንጀል ጉዳዮች አንፃራዊ ልዩነቶች ተጣበዉ ተቀራራቢ የሆነ ዉሳኔ ሊወሰንባቸዉ አይቻልም ማለት አይደለም።
    - ስለዚህ ይህ መርህ ፍርድ ቤቶች እንደፈለጉት ወይም እንዳሻቸዉ ቅጣት ከመጣል ገታ በማድረግ ወጥ የሆነና በየጊዜዉ መሻሻል የሚታይበት እንዲሆን ያስችላል ።

- **አድሎ የሌለበት/Fairness/:-**
    - ብዙ ዓይነት የማህበረሰብ ክፍል ባለበት አገር በፍትህ አካላት ዘንድ የሀሳብ ወደ አንድ ወገን ማጋደል እንዳይከሰት የቅጣት አወሳሰን መርህ ክልከላ ያደርጋል ተብሎ ይገመታል።
    - ስለዚህ በዘር፣ በፖሊቲካ፣ በፆታ፣ በኃይማኖት፣ በሀብት ደረጃ እና በመሳሰሉት መነሻ ልዩነት ሳይደረግ ቅጣት መጣል እንዲቻል ያደርጋል ማለት ነዉ።
- **ግልፅነት/Transparency/:-**
    - ግልፅነትና ተጠያቂነት አብረዉ የሚሄዱ መርሆዎች ናቸዉ።
    - በመሆኑም ዳኞች ዉሳኔቸዉን በምክንያት ለማስደገፍ ይገደዳሉ።
    - በምክንያት ማስደገፍ ግዴታ ሆኖ በተጨማሪም የሚያቀርቡት ምክንያቶች ቅጣት ለማክበድም ሆነ ለማቅለል ግልፅነት ያለዉ መሆን ይጠበቅባቸዋል።
    - የቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ እነዚህን ምክንያቶች ለአጠቃቀም በሚመች መልኩ በግልፅ በማስቀመጥ ሌሎች የህብረተሰብ አካላትም በግልጽ አይተዉት መገመት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል ማለት ነዉ።
    - በተጨማሪም የግልፅነት መርሆዉ የዳኞችን የተጠያቂነት አድማስም ያሰፋል ማለት ነዉ።

# የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በኢትዮጵያ

- ከቅጣት አመዳደብ ስርዓት ጋር በተያያዘ ለዳኞች ሰፋ ያለ ፍቅድ ስልጣን (discretion) መስጠት በራሱ ችግር አይደለም፡፡
- ከታሪክ መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ የተወሰነ ቅጣት ብቻ በማስቀመጥ የዳኞችን ፍቅድ ስልጣን መገደብ የወንጀል ህግ ዓላማና ግቦችን የሣተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ስለዚህ ዳኞች አመዛዝነው የመወሰን ስልጣን እንዲኖራቸው ማድረጉ ያለንበት ዘመን የጠየቀው ተገቢ አሠራር ነው፡፡
- ነገር ግን ይህ አሰራር የሚያበረክተው ጥቅም እንዳለ ሆኖ ደካማ ጐኖችም ያሉት ነው፡፡
- በተለይም በተቀመጠው ሰፊ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ ቅጣት እንዴት እንደሚወሰን ግልፅ አሰራር በሌለባቸው አገሮች በተመሣሣይ ጉዳዮች ያልተገባ የቅጣት ልዩነት ስለሚከሰት የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩን ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ሆኗል፡፡

- በመሆኑም እነዚህን ውስንነቶችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ አማራጮችን ተግባራዊ ማድረግ የማይታለፍ ስራ እየሆነ መጥቷል፡፡
- ከነዚህ መካከል አንዱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያን በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ ነዉ፡፡
- አሁን ባለንበት ዘመን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አዲስ ነገር አይደለም፡፡
- በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስራ ዉስጥ የቅጣትን ፍትሀዊነት ማረጋገጥ የብዙ ሀገራት ቀዳሚ አጀንዳ እየሆነ መጥቷል፡፡
- በተለይ የኮመን ሎው የህግ ስርዓት ተከታይ በሆኑ አገራት ውስጥ በተነፃፃሪ ዝርዝር የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ የማድረግ ተሞክሮና ልምድ አለ፡፡
- በኛ ሀገር ሁኔታም በጠቅላላ መርሀዎች ብቻ ችግሩን ሙሉ ለሙሉ መፍታት አልተቻለም፡፡

- ስለዚህ ቅጣትን ወጥና ትክክለኛ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በህግ አውጭው ተወስኗል፡፡
- ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከማለፋችን በፊት የቅጣት አወሳሰንን መመሪያ አስፈላጊነት በተመለከተ ህግ አውጭው ባደረገው ውይይት ያነሳቸውን መሠረታዊ ኃሳቦች ማዬቱ ጠቃሚ ነዉ፡፡
- የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አስፈላጊነት ላይ ባደረገው ውይይት፡-
  - በወንጀል ህጉ ላይ የቅጣት መነሻ እና መድረሻ መቀመጡንና የተለያዩ የቅጣት አማራጮችም መኖራቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት
  - የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቢያወጣ የተሻለ መሆኑንና
  - ከዚህ አኳያ እያንዳንዱ ዳኛ የሚሰጠው ፍርድ አንድ ዓይነት ባይሆንም ወጥነትና ተመጣጣኝነት እንዲኖረው የማንዋሉ መውጣት አስፈላጊ መሆኑን ገልፆ፣
  - ይህ ሲባል ግን ሌላ የወንጀል ህግ ይወጣል ማለት እንዳልሆነ አስምሮበታል፡፡

- ከዚህ ውይይትና መደምደሚያ መረዳት የምንችላቸው በርካታ ቁምነገሮች አሉ፡፡
  - የመጀመሪያው መመሪያው ዳኞች አንድ ዓይነት ፍርድ እንዲሰጡ ሊያደርግ የሚችል አለመሆኑን ነዉ፡፡
  - ይህ ሃሳብ የሚመነጨው ከሀገራችን የወንጀል ቅጣት አመዳደብና አጣጣል ስርዓት ነው፡፡
  - እንደሚታወቀው በኛ አገር ተቀባይነት ያገኘዉ አሰራር የቅጣት መነሻና መድረሻው በህግ አውጭው ከተወሰነ በኃላ በተቀመጠዉ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ ዳኞች የነገሮችን ሁኔታ መዝነው ተመጣጣኝ ያሉትን ቅጣት የሚወሰኑበት ነው፡፡
  - ስለዚህ በተመሣሣይና ተቀራራቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በተቻለ መጠን የተቀራረበ ቅጣት ለመጣል የሚያስችል ስርዓትን መዘርጋት የህግ አዉጭዉ ፍላጎት ነዉ፡፡
  - ነገር ግን ተመሳሳይ ጉዳዮች ቢሆኑም ዳኞች ልዩ ሁኔታዎችን የማመዛዘን ኃላፊነት ያለባቸዉ በመሆኑ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ቅጣት ይወሰናል ተብሎ አይታሰብም፡፡

- **ሁለተኛው** መሠረታዊ ነጥብ ደግሞ መመሪያዉ የወንጀል ህጉ ማስፈፀሚያ እንጂ ሌላ ህግ የሚያቋቁም አለመሆኑ ነው፡፡
- የቅጣት አወሳሰንን መመሪያ ሲቀረፅ እጅግ ጥንቃቄ ከሚጠይቁ ጉዳዮች መካከል አንዱ ከህግ አውጭ ሃሳብ ውጭ የሆኑና በወንጀል ህግ ውስጥ ያልተመለከቱ ፍሬነገሮች እንዳይከተቱ በማድረጉ ላይ ነው፡፡
- ህግን ለማውጣት ስልጣን ያለው አካል ይሁንታ ያልሰጠባቸዉን ጉዳዮች በመመሪያ ማካተት ተቀባይነት የለዉም፡፡
- ስለዚህ ችግር እንዳይከሰት በዝግጅት ወቅት  ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባ ሲሆን ይህ ባጋጣሚ ከተከሰተም ዳኞች መመሪያውን በመተዉ በወንጀል ህጉ መሰረት የመወሰን ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡
- **ሶስተኛው** ነጥብ ደግሞ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ሌላው አስፈላጊነት ቅጣት ተገማች እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡
- አንድ ተከሣሽ ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ የመነሻ ቅጣቱ የት ላይ ሊያርፍ እንደሚችል፣ ማክበጃና ማቅለያዎች ከቀረቡ ሊኖር የሚችለውን የቅጣት ጭማሪ እና ቅናሽ ማወቅ እንዲችል ያግዛል፡፡

# መመሪያዉ ትኩረት የሰጠባቸዉ መሠረታዊ ጉዳዮች

1.የወንጀል ደረጃዎችን ማዘጋጀት

- በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት የወንጀል ደረጃ ማለት በወንጀል አፈፃፀም ባህሪያቸው እና ከባድነታቸው አንፃር የቅጣት አወሳሰን በተመሳሳይ ደረጃ ለማስቀመጥ እንዲቻል የወንጀል ድርጊት መመዘኛዎችን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጅ ደረጃ ነው፡፡
- እንደሚታወቀዉ ህግ አውጭው በመነሻና መድረሻው መካከል ሰፊ ፍቅድ ስልጣን ያስቀመጠበት ምክንያት በተመሣሣይ ድንጋጌ ጥፋተኛ በተባሉ ሰዎች ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠን የተለያየ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ነው፡፡
- ስለዚህ በአንድ ድንጋጌ ውስጥ የተለያዩ የወንጀል ደረጃዎች እንዳሉ መረዳት ይቻላል፡፡
- ይህንን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የወንጀል ህጉን የተወሰኑ ድንጋጌዎች በምሣሌነት እንመልከት፡፡

- የወንጀል ህጉ አንቀፅ 407(2) በስልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡
- በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ የተባለ ሰው ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራትና ከሃምሣ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይችላል፡፡
- የእስራት ቅጣቱን ብቻ እንኳ ለይተን ብንመለከት በሰባት እና አስራ አምስት ዓመት መካከል ሰፊ ፍቅድ ስልጣን አለ፡፡
- አንዳንድ ድንጋጌዎች ደግሞ ከዚህም አልፈው እስከ ሃያ አምስት ዓመት ድረስ ፍቅድ ስልጣን የተቀመጠላቸው ናቸው፡፡
- ህግ አውጭው ይህንን ሰፊ ፍቅድ ስልጣን ያስቀመጠበት ምክንያት የወንጀል ፈፃሚዎች የግል ሁኔታና የወንጀል አፈፃፀም ደረጃ የተለያየ ሊሆን እንደሚችል ግምት ውስጥ አስገብቶ ነዉ፡፡

- በህጉ የተመለከቱትን መመዘኛዎች በመጠቀም ጥፋተኛ ለተባሉ ሰዎች ደረጃ በማውጣት ቅጣት መወሰን ለዳኞች አዲስ ነገር አይደለም፡፡
- ከመመሪያው በፊት ከነበረው ልምድ መረዳት እንደሚቻለው ዳኞች የተፈፀመው ወንጀል ከባድ በመሆኑ ቅጣቱ ከፍ ብሎ እንዲወሰን መደረጉን፣ በአንፃሩ ቀላል ሆኖ ሲያገኙትም ይህንኑ በመግለፅ ተመጣጣኝ ነው ያሉትን ቅጣት እንደወሰኑ በመዝገብ ይገልፃሉ፡፡
- ስለዚህ የመመሪያው ትኩረት አዲስ ሃሳብ ማምጣት ሳይሆን ዳኞች ለአንድ ወንጀል አፈፃፀም በየራሳቸው የሚሰጡት ክብደት የተለያየ በመሆኑ ይህንን ለመቀነስና ለማቀራረብ የሚያስችል ስርዓትን ለማጠናከር ነው፡፡
- ነገር ግን ይህ ጥሩ ፍላጎት ቢሆንም ወደ ተግባር ለመለወጥ ቀላል አይደለም፡፡
- በቅድሚያ ህጉን ብቻ መሰረት ያደረጉና አሳማኝ ደረጃዎችን ለማዘጋጀት በሚያስችሉ መርሆዎች ላይ መግባባትን ይጠይቃል፡፡

- በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደተሞከረዉ የወንጀል ደረጃዎች  በድንጋጌው ውስጥ የተቀመጡትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ መዘጋጀት አለባቸዉ።
- ይህንን አንድ ምሳሌ በማንሳት ግልፅ ማድረግ ይቻላል።
- በአንቀፅ 47ዐ(2) ውስጥ የተቀመጡትን ፍሬ ነገሮች ስንመለከት፦
  - ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣
  - የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣
  - የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም
  - የደረሰው ጉዳት መጠን በፍሬ ነገርነት የተጠቀሱ ናቸው።
- እነዚህን ፍሬ ነገሮች በማረጋገጥ የምናገኘው ውጤት መነሻ ቅጣቱን ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደረግ የሚችል ነው።
- ለምሣሌ  ወንጀሉ የፈተፀመው በከባድ ዓላማ ከሆነ፣ የስልጣን ደረጃው ከፍተኛ ከሆነ ወይም በድንጋጌው እንደተገለፀው በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ወይም ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ መነሻ ቅጣቱም በዚያው ልክ ከፍ ብሎ መወሰን ይኖርበታል።
- ከዚህ በተለየ ሁኔታ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሆኖ ከተገኘ ደረጃው ዝቅ ብሎ ይቀመጥና መነሻ ቅጣቱም በዚያው መጠን ዝቅ ይላል።
- በመሆኑም ለእያንዳንዱ ድንጋጌ የወንጀል ደረጃዎችን ማዘጋጀት በቅጣት ላይ የሚታዩ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ የሚያስወግድ ባይሆንም ልዩነቶችን ትርጉም ባለው ሁኔታ ለመቀነስ የሚያስችል ነው።

- ይሁን እንጂ ህግ አውጭው ባስቀመጣቸው ፍሬ ነገሮች ማዕቀፍ ውስጥ በመሆን ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ችግሮች ያጋጥማሉ፡፡
- ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት በሙስና ወንጀሉ የተገኘውን ጥቅም ከፍተኛ፣ መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ ነው ለማለት የሚያስችል በህግ አውጭው የተቀመጠ መጠን የለም፡፡
- ወንጀሉ የተፈፀመበት ዓላማም ከባድ መሆን አለመሆኑ
- እንዲሁም የወንጀል አድራጊው የስልጣን ደረጃ ከፍተኛ፣ መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ መሆኑን መለየትም ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው፡፡
- እነዚህን ለማዘጋጀት የወንጀል ህጉን ብቻ ሣይሆን ሌሎች ህጐችን ጭምር መመልከት አስፈላጊ ነዉ፡፡
- ስለዚህ በወንጀል ፈፃሚዎች ላይ ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን የእያንዳንዱን ድንጋጌ ይዘት በሚገባ በመመርመር ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ድረስ ሊኖር የሚችለውን ደረጃ ማዘጋጀት እንዲሁም  የህግ ማዕቀፎችን በተሟላ ሁኔታ  መመርመር የሚያስችል ሰፊና ጥልቀት ያለው ጥናት ማድረግ  ያስፈልጋል፡፡

- የወንጀል ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ሌላው የሚያጋጥም ችግር ከድንጋጌዎች ባህሪ ጋር የሚያያዝ ነው።
- በአንዳንድ ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱ ፍሬ ነገሮች ግልፅ ካለመሆናቸው በተጨማሪ ፍሬ ነገሮቹ ግልፅ ናቸው ብለን ደረጃ ብናዘጋጅ ውጤቱ ያልተፈለገ ሊሆን ይችላል።
- ለምሣሌ የስርቆት ወንጀልን እንመልከት።
- የወንጀል ህጉ አንቀፅ 665(1) ማንም ሰው የማይገባውን ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የሌላውን ሰው ንብረት የሆነውን ተንቀሳቃሽ ዕቃ ወይም ከማይንቀሳቀስ ንብረት የነጠለ፣ ዕቃ አንስቶ የወሰደ፣ በቀጥታ የራሱ ንብረት ያደረገ ወይም በተዘዋዋሪ ከራሱ ንብረት ጋር እንዲቀላቀል ያደረገ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እንደሚቀጣ ይደነግጋል።

- ይህ ድንጋጌ በንብረት ወይም ገንዘብ መጠን ላይ የሚመሠረት መሆኑን ታሣቢ በማድረግ ደረጃዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሲሆን ውጤቱ ያልተጠበቀ ነበር፡፡
- የወንጀል ደረጃው የተመሠረተው በገንዘብ መጠን ላይ ብቻ በመሆኑ የአጥፊዎቹን ሃሳብ ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዳደረገውና የተሰረቀው ገንዘብ አነስተኛ ነው በሚል ብቻ ደረጃው ዝቅተኛ ስለሚሆን የሚጣለው ቅጣት አስተማሪ መሆኑ ቀርቶ በተቃራኒው ተመሣሣይ ወንጀል ፈፃሚዎችን የሚያበረታታ ነው የሚል ትችት ሲቀርብ ነበር፡፡
- መመሪያ ቁጥር 2 ለማዘጋጀት በተካሄደ አጭር ጥናትም ይህ ችግር እንደነበር ተረጋግጧል፡፡
- ስለዚህ ተመሣሣይ ችግሮች እንዳያጋጥሙ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግና ይህ ሁሉ ተደርጎ የሚያጋጥሙ ከሆነም እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉ አሠራሮችን ማበጀት ያስፈልጋል፡፡

- ደረጃ ለማዘጋጀት አስቸጋሪ የሆኑ ድንጋጌዎች በሚኖሩበት ጊዜ ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ከመሞከር ይልቅ ዳኞች የነገሩን ሁኔታ እያዩ ደረጃውን በመወሰን መነሻ ቅጣት እንዲወስኑ ማድረግ አንዱ አማራጭ ነው፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ ደረጃ ለማውጣትና መነሻ ቅጣትን መወሰን አስቸጋሪ ከሆነ ይህንኑ በመጥቀስ ከመመሪያው ውጭ መወሰን የሚቻልበትን አሠራር መፍቀድ ያስፈልጋል፡፡ ይህ አሰራር የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተግባራዊ ባደረጉ አገሮቸ የተለመደና በኛ አገር ሁኔታም በተመሳሳይ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሞከረ ያለ ነዉ፡፡
- የወንጀል ደረጃዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ጥንቃቄ ከሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች መካከል መጠቀስ ያለበት ሌላም መሠረታዊ ጉዳይ አለ፡፡
- ይህም በአንዳንድ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ውስጥ የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች ለቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያ ምክንያትነት የሚጠቀሱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- እነዚህን እንዳሉ የምንጠቀምባቸው ከሆነ የህጉን አላማና ግቦች ማሣካት አይቻልም፡፡

- ጉዳዩን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ አሁንም የተወሰኑ ድንጋጌዎችን በማንሳት እንመልከት፡፡
- በወንጀል ህጉ ከአንቀፅ 545-552 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፅንስ ላይ የሚደረግ ወንጀልን የሚመለከቱ ናቸው፡፡
- ከነዚህ መካከል በአንቀፅ 548 ላይ እንደተገለፀዉ የፅንስ ማስወረድ ተግባር የተፈፀመው በህግ ከተደነገገው ውጭ እንደሆነና በተለይ ጥፋተኛው ወንጀሉን ያደረገው፡-
  - በአፍቅሮ ንዋይ ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም የዘወትር ተግባሩ በማድረግ እንደሆነ፣
  - ወንጀሉ የተደረገው በቂ የህክምና ሙያ በሌለው ሰው ከሆነ
  - እንዲሁም ወንጀሉን ያደረገው ባለሙያ በተለይ ሀኪም፣ መድሃኒት ቀማሚ፣ አዋላጅ፣ ወይም አስታማሚ ሆኖ የሙያ ሥራውን ያለአግባብ በመገልገል ድርጊቱን የፈፀመ ከሆነ ቅጣቱ ከብዶ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡

- የድንጋጌዉን ይዘት ስንመለከት አፍቅሮ ንዋይ፣ ድርጊቱን የዘወትር ተግባሩ ማድረግ እና የመሳሰሉትን ፍሬ ነገሮች እናገኛለን፡፡
- እነዚህ ደግሞ በህጉ አንቀፅ  84 ስር የማክበጃ ምክንያቶች ተብለዉ የተዘረዘሩ ናቸው፡፡
- በተመሳሳይ ሁኔታ አንዳንድ ድንጋጌዎች የማቅለያ ምክንያቶችን አካተዉ ልናገኝ እንችላለን፡፡
- ለምሳሌ  በወንጀል ህጉ ከአንቀፅ 553-559 ድረስ የተዘረዘሩት በሰው አካልና ጤና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል አንቀፅ 557 ማንም ሰው በሌላ ሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ አስቦ ጉዳት ያደረሰው አስገዳጅ ሁኔታን በመተላለፍ ወይም ህጋዊ መካላከልን ከመጠን በማሣለፍ እንደሆነ ወይም ከፍ ባለ ደም በሚያፈላ ምክንያት ባልጠበቀው ህሊናን በሚያውክ ድንገተኛ ምክንያት ወይም ከፍተኛ ስሜት ወዘተ... እንደሆነ ቅጣቱ ቀልሎ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡

- ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ለአብነት ያህል ይቅረቡ እንጂ ተመሳሳይ የሆኑ በርካታ ድንጋጌዎች እንዳሉ ልብ ማለት ይገባል።
- እነዚህ ምክንያቶች በአንድ በኩል ደረጃዎችን ለማዘጋጀት በሌላ በኩል ደግሞ ከመነሻ ቅጣት በኋላ በማክበጃ ወይም በማቅለያ ምክንያትነት በድጋሜ የምንጠቀምባቸው ከሆነ ቅጣትን ያለ አግባብ የሚያቀሉ ወይም የሚያከብዱ በመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።
- በአጠቃላይ በመመሪያዉ ትኩረት የተሰጠዉ አንዱ ስራ  የወንጀል ደረጃዎችን ማዘጋጀት ነዉ።

. የመነሻ ቅጣት አወሳሰንን ማቀራረብ

- የቅጣት አወሳሰንን ወጥነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከሚረዱ ጉዳዮች መካከል አንዱ የመነሻ ቅጣት አወሳሰን ተቀራራቢ እንዲሆን ማድረግ ነው።
- በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት መነሻ ቅጣት ማለት ቅጣቱን የሚያቀሉ እና የሚያከብዱ ጠቅላላ እና ልዩ ምክንያቶች ታሳቢ ከመደረጋቸው በፊት በፍርድ ቤቱ የቅጣት እርከኑን መሠረት በማድረግ የሚጣል ቅጣት ነው።
- ከዚህ በመቀጠል የሚነሳዉ ጥያቄ ህጉ ካስቀመጠው በተለየ ሁኔታ የመነሻ ቅጣት አወሳሰን ስርዓት ማበጀት አስፈላጊ ነው ወይ የሚለውን ሲሆን ለጥያቄው ምላሽ የምናገኘው የወንጀል ህጉን በመመልከት ነዉ።
- የወንጀል ህጉ አንቀፅ 189(1) እንደሚያመለክተው በአንድ ወንጀል ላይ ቅጣትን የሚያከብዱ እና የሚያቀሉ ጠቅላላ ምክንያቶች በተደራረቡ ጊዜ ፍርድቤቱ አስቀድሞ ማክበጃ ምክንያቶችን ከግምት በማስገባት ቅጣቱን ያከብድ እና ቀጥሎ የሚያቀልሉትን ምክንያቶች መሠረት አድርጎ ቅጣቱን ይቀንሳል በማለት ይደነግጋል።

- በዚህ ድንጋጌ መሠረት እንደነገሩ ሁኔታ ቅጣትን ለማክበድም ሆነ ለማቅለል መጀመሪያ የምንነሳበት ቅጣት መኖር አለበት።
- መነሻ የሚያስፈልገው የምንነሳበትን አውቀን ለማክበድ ወይም ለማቅለል ነው።
- ምንም እንኳን ይህ ድንጋጌ የተሟላ ባይሆንም የሚታየዉን ወጥነት የሌለዉ አሰራር ለመቀየር መነሻ ሊሆን የሚችል ነዉ።
- የቅጣት አወሳሰንን መመሪያው ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት የመነሻ ቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ በፍርድ ቤቶቻችን ወጥ የሆነ አሠራር አልነበረም።
- በአብዛኛው እንደሚታየው ፍ/ቤቶቻችን መነሻ ቅጣቱ እንዴት እንደተወሰነ ሳይገልፁ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ተቀብለው ተገቢ ነው ያሉትን ቅጣት ይወስናሉ።
- በዚህ አሰራር ቅጣቱ ከየት ተነስቶ እንደከበደ ወይም እንደቀለለ በግልፅ የማይቀመጥ ከመሆኑም በላይ በግምት ላይ የሚመሠረት በመሆኑ ወጥነትንና ትክክለኛነትን ማረጋገጥ አላስቻለም።

- አንዳንድ ዳኞች ደግሞ የመነሻ ቅጣት መወሰን አስፈላጊ መሆኑን ተስማምተዉ ነገር ግን ድንጋጌው ያስቀመጠውን ቅጣት አማካይ መነሻ መሆን አለበት ብለው የሚያምኑና ተግባራዊ የሚያደርጉ አሉ፡፡
- ይህ ዘዴ በጥቅል ሲታይ የተሻለ ቢመስልም የራሱ ውስንነቶች ያሉበት ነው፡፡
- ከውስንነቶቹ መካከል አንዱ ለሁሉም ወንጀል ፈፃሚዎች ተመሣሣይ የሆነ መነሻ ቅጣት መያዝ ውጤቱን ፍትሃዊ ሊያደረግ አይችልም የሚል መከራከሪያ ይነሳል፡፡
- ስለዚህ ለዝቅተኛ የወንጀል አፈፃፀም ዝቅተኛ መነሻ፣ ለመካከለኛና ከፍተኛም በዚሁ አግባብ ከፍ እያለ የሚሄድ መነሻ ቅጣት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል አሠራር መዘርጋት የተሻለ አማራጭ ሆኖ በመገኘቱ በመመሪዉ ዉስጥ እንዲካተትበት ተደርጓል፡፡

- በወንጀል ህጉ አንቀፅ 88(3) ላይ እንደተገለፀው የህጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፍርድ ቤቶች እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ተገቢ የሆነውን ቅጣት መወሰን አለባቸው፡፡
- የተጠቀሰው ድንጋጌ ስለመነሻ ቅጣት አወሳሰን በቀጥታ ባይገለፅም ምንጊዜም ቢሆን ለአንድ የወንጀል ድርጊት ከተቀመጠው ዝቅተኛ ቅጣት ጀምሮ ወደሚቀጥለው ደረጃ ማድግ እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡
- ይህንን አስመልክቶ ህግ አውጭው ባደረገው ውይይት ድንጋጌው በወንጀል ህጉ ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣል ተብሎ መገመቱንና ዳኞችም ቅጣት ሲወስኑ በልዩ ሁኔታ የተደነገጉ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው በተቻለ መጠን ከዝቅተኛው መጀመር እንዳለባቸው ገልጿል፡፡
- ስለዚህ ህጉ በግልፅ ያስቀመጠው መነሻ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚሁ አግባብ ደረጃውን በመከፋፈል ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

- ይህ አሰራር የመነሻ ቅጣት አወሳሰንን ሊያቀራርብ የሚችል የተሻለ አማራጭ ነው፡፡
- ትኩረት መደረግ ያለበት  ፍቅድ ስልጣንን የበለጠ በማጥበብ ላይ ሣይሆን የመነሻ ቅጣቱን መጠን ለመወሰን የሚያስችሉ ጠቋሚ መመዘኛዎችን በማካተት ላይ ነው፡፡
- እነዚህ መመዘኛዎች ከማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ውጭ ያሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
- ዳኞች በመነሻ ቅጣት መወሰኛ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ ሲወስኑ በተጨባጭ በክርክር ወቅት የተገናዘቧቸውን እውነታቸው (Facts) መሠረት አድርገው መሆን አለበት፡፡
- እነዚህ እውነታዎች ደግሞ እንደሚቀርቡት ጉዳዮች የተለያዩ መሆናቸው አይቀርም፡፡
- ስለዚህ መነሻ ቅጣትን ለመወሰን በተሰጠው ጠባብ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ለመወሰን አሣማኝና በምክንያት የተደገፈ ትንታኔ ከዳኞች የሚጠበቅ ነው፡፡
- ይህ ከሆነ አሰራሩ እየተጠናከረና የበለጠም ግልፅ እየሆነ ይሄዳል፡፡
- በአጠቃላይ የመነሻ ቅጣት አወሳሰንን ግልፅ ማድረግ ሊታለፍ የማይገባ ሥራ በመሆኑ በመመሪያዉ ውስጥ ትኩረት አግኝቷል፡፡

## 3. የማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች አጠቃቀምን ወጥ ማድረግ

- የወንጀሉ ደረጃ ከተለየና የመነሻ ቅጣት ከተወሰነ በኃላ የቅጣት ሃሳብ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡
- በዚህ ወቅት በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርቡ የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች የመጨረሻዉ ቅጣት ከተያዘው መነሻ ከፍ ወይም ዝቅ ብሎ እንዲወሰን የሚያደርጉ ናቸው፡፡
- በአንድ የወንጀል ህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች ቅጣት ሊለያይ ወይም ሊቀራረብ የሚችለው በሚቀርቡና ተቀባይነት በሚያገኙ የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ብዛትና ዓይነት መለያዬት መሆኑ ይታወቃል፡፡
- የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ግብ በአጥፊዎች ላይ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እንዲጣል ማድረግ ሲሆን ውጤቱ ዞሮ ዞሮ የወንጀል ህጉን ዓላማና ግቦች ማሳካት ነው፡፡
- እነዚህን ደንቦች በመጠቀም እንደነገሩ ሁኔታ ቅጣትን በልዩ ወይም ጠቅላላ ክፍል እስከተመለከተው ጣሪያ ድረስ ማክበድ ወይም ህግ አውጪው ባስቀመጠው መርህ መሰረት ለቅጣቱ ዓይነት ዝቅተኛ ተብሎ እስከተመደበው ቅጣት ድረስ በመውረድ ማቅለል ይቻላል፡፡
- የማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች የወንጀል ህጉን ዓላማና ግቦች ለማሳካት ወሳኝ የመሆናቸውን ያህል በአግባቡ ስራ ላይ የማይውሉ ከሆነም ስራዉን የሚያዛቡ ናቸው፡፡

- የቅጣት ይህንን አስመልክቶ አንድ ምሁር በምርምር ፅሁፋቸዉ የገለፁትን እንመልከት።
- If sentencing factors are not conceptually and systematically applied, the public image of sentencing will suffer. Poorly understood sentencing factors can be the source of much public and media criticism.
- ይህ ሃሳብ በግርድፉ ወደ አማርኛ ሲመለስ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን በአግባቡ ተገንዝቦ መጠቀም ካልተቻለ ማህበረሰቡ በቅጣት ላይ እምነት እንዳይኖረዉ ያደርገዋል የሚል ነዉ።
- ቅጣት ሊከብድ በማይገባው ሰው ላይ የሚከብድ ከሆነ ወይም በተቃራኒው የሚቀል ከሆነ ችግሩ በጥፋተኛው ላይ ብቻ ሣይሆን በማህበረሰቡም ላይ ይንፀባረቃል።
- እነዚህ ምክንያቶች በጥቅሉ ሲታዩ በቀላሉ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ቢመስሉም በተግባር አስቸጋሪ መሆናቸውን እናያለን።

- ህግ አውጪው በተወሰነ መልኩ ምክንያቶችን ለመዘርዘር ጥረት አድርጓል፡፡
- ይሁን እንጂ በማህበረሰቡ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ለውጥና በእያንዳንዱ ጉዳይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከወዲሁ ሙሉ ለሙሉ ለመገመት አስቸጋሪ ነዉ፡፡
- በመሆኑም ፍትህን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለዉን የዳኞችን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን ለመጠበቅ ሲባል በህግ ያልተዘረዘሩ ምክንያቶች ባጋጠሙ ጊዜ ፍርድቤቱ ምክንያቱን በመግለፅ ሊጠቀምባቸው እንደሚችል በህግ ተደንግጋል ፡፡
- ስለዚህ ምክንያቶቹ በህግ ተዘርዝረው የተቀመጡ ወይም ያልተቀመጡም ቢሆንም አሳማኝ እስከሆኑ ድረስ ዳኞች ፅፈው የሚጠቀሙባቸው በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡
- ይህ በመሆኑ የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ብዛት ይህን ያህል ነው ብሎ መናገር አይቻልም፡፡

- የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች በሚል በጥቅሉ የሚጠቀሱ ቢሆኑም ይዘታቸውን ስንመረምርም የተለያዩ ናቸው፡፡
- ማክበጃ ብለን በምንጠራው ውስጥ ጠቅላላና እና ልዩ እንዲሁም ማቅለያዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተከፋፍለው የሚቀመጡ ናቸዉ፡፡
- ይህ ክፍፍልም ቅጣትን ለማክበድ እንዲሁም ለማቅለል የምንሰጠውን ዋጋ ጭምር የሚጠቁም ነው፡፡
- ስለዚህ ብዛታቸዉን ብቻ ሣይሆን ይዘታቸውንም በአግባቡ አለመረዳት የሚያጋጥም ችግር ነዉ፡፡
- በተለይመ የህግ ሞያ የሌላቸዉ ተከራካሪ ወገኖች የትኛው ምክንያት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው፣ የትኛው ምክንያት መቅረብ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት በአግባቡ ያለመገንዘብ እንዲሁም ህጉ በሚፈቅደው አግባብ አለማስረዳት ችግር ያጋጥማል፡፡

- የቅጣት አወሳሰን መመሪያው ሥራ ላይከመዋሉ በፊት የነበረውን የቅጣት አወሳሰን ልምድ ስንመለከት የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱን በማክበድም ሆነ በማቅለል ያላቸውን ዋጋ በግልፅ ለማወቅ አይቻልም፡፡
- የውሣኔ መዛግብትን ስንመረምር የምናገኘው የቀረቡትን የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ግምት በማስገባት ተገቢ ነው ያልነውን ቅጣት ወስነናል የሚለውን የተለመደ አገላለፅ ነው፡፡
- በዚህ ምክንያት የተለያዩ ዳኞች ለአንድ ተመሣሣይ ጉዳይ የሚሰጡት ግምት የተለያየ ስለሚሆን ሰፊ የቅጣት ልዩነት የተለመደ ነው፡፡
- ከችሎት ችሎት ወይም ከዳኛ ዳኛ ይቅር እና አንድ ዳኛም በተመሣሣይ ጉዳይ በተለያዩ መዛግብት ላይ የሚሰጣቸው ውሣኔዎች የተራራቁ ሆነው እናገኛለን፡፡
- እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ያለው አማራጭ የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን አጠቃቀም ግልፅና ወጥ ማድረግ ነው፡፡

- የተሻሻለዉ መመሪያው አንድ ጠቅላላ የማክበጃ ምክንያት በተገኘ ጊዜ አንድ እርከን ከፍ ማድረግ እንዲችል ማቅለያ ከተገኘም በተመሣሣይ ለመቀነስ የሚያስችል አሠራርን ዘርግቷል፡፡
- ልዩ የማክበጃና የማቅለያ ምክንያቶች ደግሞ በህጉ በግልፅ የተቀመጡ በመሆኑ ባሉበት ሁኔታ ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡
- ስለዚህ ችግሩን ሙሉ በሙሉ የሚፈታዉ ባይሆንም ቢያንስ ከግምታዊ አሰራር የተሻለ ነዉ፡፡

## 4. በቅጣት አወሳሰን ላይ የሚሣተፉ አካላትን ድርሻ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ

- ተከሣሹ ጥፋተኛ ነው በተባለ ጊዜ ስለቅጣት ማክበድ ወይም ማቅለል ዐቃቢሕጉ ያለውን አስተያዬት እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱ ይጠይቀዋል፡፡
- የህጉን ዓላማና ግቦች ማሣካት እስከቻለ ድረስ ቅጣት ሊከብድባቸው በሚገቡ ጥፋተኞች ላይ በህጉ አግባብ ከብዶ እንዲወሰን እንዲሁም ሊቀልላቸው የሚገቡ ጥፋተኞች ካሉም እንዲቀልላቸው ወጥ የሆነ የክርክር ሃሳብ ማቅረብ የዐቃቢ ሕግ ተግባር ነው፡፡
- ይህንን ታሳቢ በማድረግ የቅጣት አወሳሰንን በመመሪያው ዐቃቢ ሕግ በቅጣት ላይ የሚኖረውን ሚና የበለጠ የሚያጠናክር አሰራር ዘርግቶል፡፡
- እስከአሁን እንደነበረው ቅጣቱ ከብዶ ወይም ቀልሎ ይወሰን ከሚለው ጥቅል አቀራረብ ወጥቶ ለማክበድ ወይም ለማቅለል የሚያስችሉ ምክንያቶችን በዝርዝር እና የሚያከብዱትን ወይም የሚያቀሉትን የቅጣት መጠን ጭምር በመጥቀስ ሃሳብ ማቅረብ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቷል፡፡

- ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኞች ወይም ጠበቆቻቸው ሃሳብ የሚያቀርቡበት በመመሪያውን መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡
- ከጥፋተኞች ወይም ጠበቆቻቸው የሚጠበቀው የመጀመሪያው ተግባር የማቅለያ ምክንያቶችን መለየት ነው፡፡
- እስከአሁን እንደነበረው በርካታ ጉዳዩችን መደርደር ሣይሆን በእርግጥም ዋጋ ሊኖራቸው የሚችሉ ምክንያቶች መሆናቸውን መለየት ይገባል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ ሁሉም ጉዳዮች እንኳን ባይሆኑም ክርክር የተነሳባቸው ወይም ክርክር ባይነሣም በፍርድ ቤቱ እምነት በማስረጃ ሊደገፉ ይገባል ሊባሉ የሚችሉ ምክንያቶች ማስረጃ እንዲቀርብባቸው ሊጠየቅ እንደሚችል አስቀድሞ በመገመት ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ይህንን ማድረግ ራስን ከመርዳት አልፎ የወንጀል ህጉን አላማና ግቦች ለማሣካትም የሚጠቅም ነው፡፡

- መመሪያውን የማውጣት ስልጣን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የተሰጠበት ዋናው ምክንያት ህግ አውጭው ከ...እስከ ትቀጣለህ ብሎ ባስቀመጠው ክልል ውስጥ ውሣኔን ማስቀመጥ የዳኝነት ሥራ በመሆኑ ይህንን ስልጣን ለሌላ አካል ወይም አስፈፃሚ አካል ሣይሆን መስጠት ያለበት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤቱ መሆን እንዳለበት ተገልጿል፡፡
- ስለዚህ ፍርድ ቤቶች እንደተለመደው የተከራካሪ ወገኖችን የቅጣት ሃሳብ አዳምጦ ከመወሰን ባለፈ የመመሪያውን አፈፃፀም የመከታተልና የሚያጋጥሙ ችግሮችን የመፍታት ኃላፊነት አለባቸው፡፡
- ከዚህ አኳያ የመጀመሪያው ስራ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ፖሊሲው እንደተመለከተው ባለድርሻ አካላትን ያሣተፈ መመሪያ ማዘጋጀትና ተከራካሪ ወገኖች እንዲያውቁት ማድረግ ነው፡፡
- ዳኞች ከመመሪያው በመውጣት የሚወስኗቸውን ጉዳዮች በመከታተል በግብአትነት መጠቀምና በተሣሣተ መንገድ ከመመሪያው በወውጣት የተወሰነ ካለም አፋጣኝ ማስተካከያ እንዲደረግበት ለማድረግ የሚያስችል የክትትል ስርዓት መዘርጋት የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ነዉ፡፡
- በአጠቃላይ በየደረጃው ያሉ የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች መመሪያው በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል መከታተልና የማሻሻያ ሃሳቦች ካሉ በማቅረብ የበኩላቸዉን ድርሻ ሊወጡ ይገባል፡፡

## 5. የቅጣት አወሳሰን የሚመራበትን ቅደም ተከተል ግልፅ ማድረግ

- በመመሪያዉ መሰረት የመጀመሪያው ስራ ተከሣሽ ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል ድንጋጌ ደረጃ የወጣለት መሆን አለመሆን መለየት ነው፡፡
- ደረጃ ያልተዘጋጀለት ከሆነ ዳኞች ደረጃውን መለየት አለባቸው፡፡ ከዚህ በኃላ ለድንጋጌው ከተቀመጡት ደረጃዎች መካከል አጥፊውን የሚመለከተው የትኛው ደረጃ እንደሆነ መለየት ነው፡፡
- ደረጃው ከታወቀ የመነሻ ቅጣቱ ከስንት እስከ ስንት ሊሆን እንደሚችል በቀላሉ ይታወቃል፡፡
- ባገኘነው ደረጃ ላይ ባለው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣት ይወሰናል፡፡
- የመነሻ ቅጣት ከተወሰነ በኃላ የሚኖረው ቀሪ ስራ የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች መመዘን ነው፡፡

# የመመሪያ ቁጥር 2/2006 አጠቃላይ ጉዳዮች

- የነባሩን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አፈፃፀምና የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በተመለከተ፡-
  - ጥናት በማካሄድ የማሻሻያ ሀሳቦችን የሚያቀርብ እና
  - በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ላይ አዲስ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ረቂቅ የሚያዘጋጅ የጥናት ቡድን እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡
- ስድስት አባላት ያሉትና የጥናት ሥራውን እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው የጥናት ቡድንም በተለይም ነባሩን የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በተመለከተ የሚካሄደውን የማሻሻያ ጥናት ሥራ ለማከናወን የተለያዩ ዘዴዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡

# ...የቀጠለ

- ከአንድ መቶ በላይ የሆኑ መጠይቆችን ለጉዳዩ አግባብነት ባላቸው ተቋማት ውስጥ በመስራት ውስጥ የሚገኙ የህግ ባለሙያዎች እንዲሞሉ በማድረግ ያላቸውን አስተያየት ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡
- በተጨማሪም የጥናት ቡድኑ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር **1/2002**ን በተመለከተ በልዩ ልዩ የህግ ባለሙያዎች የተዘጋጁ ጥናታዊ ጽሁፎችን በማፈላለግና በማሰባሰብ ለጥናት ሥራው በግብዓትነት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡
- የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ዝግጅትንና አተገባበር ጋር በተያያዘ ሌሎች አገራት ያላቸውን ልምድና ተሞክሮ እንዳስፈላጊነቱ በኢንተርኔት መረጃ መረብ በመጠቀም ለጥናት ሥራው ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

# …የቀጠለ

- በሌላ በኩል የጥናት ቡድኑ የማሻሻያ ጥናት ሥራውን ምሉዕ እንዲሆን ለማስቻል መመሪያው ሽፋን የሰጣቸውን የወንጀል ድንጋጌዎች በተመለከተ በፌዴራል ፍ/ቤት ደረጃ የሚሰጡ ውሣኔዎችን (ፍርዶችን) በማሰባሰብ ለጥናት ሥራው በግብዓትነት እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡
- ከጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የበርካታ አገራት የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ዝግጅት ላይ የመሣተፍ እድል የነራቸውና በዘርፉም አግባብነት ያለው የትምህርት ዝግጅት ያላቸውና የዉጭ አገር ባለሙያ አማካኝነት በተዘጋጀ የስልጠናና የውይይት መድረክ ጠቃሚ ሀሳቦችን በመውሰድ ለጥናት ሥራው በግብዓትነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

# ...የቀጠለ

- ከዚህ በላይ የተመከቱትን የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የተገኙና የተሰበሰቡ ግብዓቶችን በአንድ ላይ በመጠቀም እንዲሁም የጥናት ቡድኑ አባላት በግልና ሁለት ሁለት ሆነው በመጣመርና ነባሩን የቅጣት አወሣሠን መመሪያ የተለያዩ ክፍሎች በመከፋፈል ብሎም አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ህጉ ማዕቀፎች በአግባቡ በማጥናት **(Legal Analysis)** በቡድን ደረጃ ለሚካሄደው ነባሩን መመሪያ የማሻሻል ጥናት ሥራ ውይይት በመነሻነት ሊያገለግል የሚችል የመመሪያውን የተለየዩ ክፍሎች የተመለከቱ መለስተኛ የጥናት ሰነዶች (ጽሁፎች) እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡
- ከዚህ በመቀጠል ለውይይት መነሻነት በሚል በቡድን አባላት የተዘጋጁ መለስተኛ የጥናት ጽሁፎችን እንዲሁም ነባሩ የቅጣት አወሣሠን መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ ጋር በተያያዘ በተዘጋጁ ዳኞችና ልዩ ልዩ ባለሙያዎች በተሣተፉባቸው የውይይት መድረኮች የተሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ ነባሩን መመሪያ ለማሻሻል በሚል የተዘጋጀን ሰነድ ጐን ለጐን በአግባቡ በቅደም ተከተል በመፈተሸና ሰፊ ውይይት በማድረግ ነባሩን የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ቁጥር **1/2002**ን የማሻሻል ሥራ ተከናውኗል፡፡

# …የቀጠለ

- መመሪያ ቁጥር 2/2005 ስድስት ክፍሎች አሉት፡፡
  - የመጀመሪያው ክፍል ጠቅላላ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን በስሩም ስያሜ፣ ትርጓሜ፣ ዓላማና ግብ እንዲሁም መሠረታዊ ድንጋጌዎችን እናገኛለን፡፡
    - ትርጓሜን በተመለከተ በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አተገባበር ላይ የተነሱ ችግሮችን ለማስተካከል የተወሰነ ማሻሻያ ከመደረጉ ውጭ ብዙም ለውጥ አልደረገበትም፡፡
      - የተደረገው ማስተካከያ ከአሁን በፊት በነበረው መመሪያ ‘ፍርድ ቤት ማለት የፌዴራልና የክልል ፍ/ቤቶች ማለት ነው’ መባሉ በተለይ የወታደራዊ ፍ/ቤቶች በሌሎች አዋጆች እና በወንጀል ሕጉ መሠረት የሚያዩዋቸውን የወንጀል ጉዳዮች ግንዛቤ አለስገባም በሚል ትችት በመቅረቡና ትችቱም ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ‘ፍርድ ቤት ማለት የወንጀል ጉዳዮችን ለመዳኘት በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል’ ማለት ነው በሚል የተደረገ ማስተካከያ ነዉ ፡፡
    - የመመሪያውን ዓላማና ግቦች የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡
      - በዚህ የመመሪያው ዓላማ የቅጣት ውሣኔ ግልፅትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ አግባብ እንዲፈፀም እንዲሁም የዉሳኔ ውጤታማነትና ተገማችነት እንዲጠናከር ለማድረግ ነው፡፡
      - ስለዚህ ጥቅል ጉዳዮችን ከማስቀመጥ ይልቅ መመሪያው ሊፈታቸው

# ...የቀጠለ

- በአንቀጽ 4/1/ ሥር እንደተመለከተው የመነሻ ቅጣት መወሰን ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡
  - ➢ የመነሻ ቅጣቱን ለመወሰን ለምሣሌ በቅጣት ስንጠረዡ ውስጥ የምናርፍበት እርከን 21 ቢሆን ፍቅድ ስልጣኑ ከ5-6 ዓመት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ መነሻውን 5 ዓመት፣ 5 ዓመት ከ3 ወር ወይም ከ6 ወር ወዘተ... ብለን ለመወሰን መመዘኛችን ምንድን ነው የሚል ሰፊ ጥያቄ ይነሣ ነበር፡፡
  - ➢ እዚህ ላይ በአንድ በኩል የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ለመነሻ ቅጣት ውሣኔ ከተጠቀምን ችግር እንደሚያስከትል የታወቀ ነው፤ ምክንያቱም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 189 እንደተደነገገው ፍርድ ቤቶች ቅጣት ሲወስኑ፡-
    - ❖ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መሠረት አድርገው ቅጣቱን ከማክበዳቸው ወይም ከማቅለላቸው በፊት ከተጣሰው የወንጀል ድንጋጌ አንጻር የወንጀሉን ባህሪ መሠረት በማድረግ በቅድሚያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) መሠረት መነሻ ቅጣቱን ይወስናሉ፡፡
    - ❖ በመቀጠልም ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳሉ፤

# ...የቀጠለ

- በመሆኑም መነሻ ቅጣት ለመወሰን  የወንጀል ሕጉን አንቀጽ **88/2**/ን መጠቀም ተገቢ ነዉ፡፡ ይህ ድንጋጌ ችግሩን ሙሉ በሙሉ የሚፈታው ባይሆንም ቢያንስ ዳኞች ወጥ የሆነ አሠራርን እንዲከተሉ የሚረዳ  ነው፡፡

- በመርህ ደረጃ በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የተደነገገው የቅጣት መነሻ ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ እንዲቻል በአንቀጹ ከተቀመጠው መነሻ ጀምሮ እንደወንጀሉ ከባድነት መነሻው ከፍ እያለ በሚሄድ መልኩ ቅጣት ይወሰናል፡፡
- ይሁንና በመመሪያ ቁጥር **1/2002** አፈፃፀም ላይ ከታዩ ችግሮች መካከል አንዱ በተለይ አንዳንድ የወንጀል ድርጊቶች (ለምሳሌ ስርቆት፣ ማታለል ...) በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚያደርሱት ተጨባጭ ጉዳት ጋር የሚመጣጠን ቅጣት ለመወሰን እንዲቻል መነሻ ቅጣቱን ከፍ ብሎ ለመወሰን የሚያስችል አሰራር አለመዘርጋቱ ነው፡፡
- በዚህ መሠረት በመመሪያ ቁጥር **2/2005** ከአንዳንድ ወንጀሎች የተለየ ባሕሪ የተነሳ ከመነሻው መጀመር ተመጣጣኝና ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ ሲገኝ መነሻ ቅጣቱ ከፍ ብሉ እንዲጀመር ለማድረግ የሚረዳ አሰራር ተከተል፡፡

# ...የቀጠለ

- የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎች በተመሳሳይና ተቀራራቢ ደረጃ ለሚገኙ የወንጀል ድርጊቶች ወጥነት ባለው መልኩ ቅጣቱን የሚያከብዱ ወይም የሚያቀሉ ይሆናሉ፡፡
- ሆኖም በወንጀል ሕጉ ስለ ልዩ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡
- ፍርድ ቤቶች መነሻ ቅጣቱን ለማስቀመጥ፣ እንዲሁም የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ለማክበድ ወይም ለማቅለል ሲወስኑ እንደ ወንጀሉ ዓይነት ሊታዩ የሚገቡ ልዩ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ በየቅጣት እርከኑ ባለው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ አግባብነት ያለውን ቅጣት መወሰን ይችላሉ፡፡
- በዚህ መመሪያ የወንጀል ደረጃ ያልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች ላይ የሚወሰነው ቅጣት በዚህ መመሪያ የወንጀል ደረጃ ለወጣላቸው የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ላይ ቅጣት ለመጣል የተቀመጡትን አጠቃላይ ድንጋጌዎች፣ መስፈርቶችና አሰራሮችን እንደሁኔታው

# …የቀጠለ

- የመመሪያው ክፍል ሁለት 3 ድንጋጌዎች ይዟል፡፡
  - ➢ አንቀጽ 5 አጠቃላይ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያሣይ ሲሆን
  - ➢ አንቀጽ 6 ነፃነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ የቅጣቶች እርከን ሰንጠረዥን የሚመለከት ነው፡፡
  - ➢ አንቀጽ 7 ደግሞ ስለገንዘብ መቀጮ ሰንጠረዥን መርሆዎች የሚዘረዝር ነው፡፡
- የሁለቱም ሰንጠረዦች ዓላማ የእስራት ቅጣትም ሆነ የገንዘብን መቀጮ ሲወሰን ወጥነትን ለማረጋገጥ የሚያችሉ አሰራሮችን መዘርጋት ነው፡፡

## ነፃነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶችና የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ

## የቅጣት እርከኖች ሠንጠረዥ

- በዚህ መመሪያ መሠረት የሚጣለው ቅጣት ለተመሳሳይና ተቀራራቢ የወንጀል ድርጊቶች ተመሳሳይ እና ተቀራራቢ ቅጣት ለመጣል እንዲቻል፣ እንዲሁም የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱን በተመሳሳይ መጠን እንዲያከብዱ ወይም እንዲያቀሉ ለማድረግ እንዲቻል ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

## ነጻነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሠንጠረዥ

- ነጻነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሠንጠረዥ ከቀላል እስራት እስከ ሞት ቅጣት ድረስ ያለውን ያካተተ ነው፡፡
- በወንጀል ሕጉ በተመለከተው መሠረት ከዝቅተኛው ቅጣት 1 ቀን የግዴታ ሥራ እስከ ከፍተኛው ቅጣት ሞት ድረስ የሚደርስ 39 የቅጣት እርከኖች ያሉት ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል፡፡

# ...የቀጠለ

- ሠንጠረዡ ሲዘጋጅ መሰረት ያደረጋቸው መሰረተ ሀሳቦች፡-
  - የቅጣት መነሻቸው ከእርከን 1 ጀምሮ እስከ ቅጣት እርከን 15 ድረስ በመነሻውና በመድረሻው መካከል የስድስት ወር ፍቅድ ሥልጣን (range) እንዲኖር ተደርጓል።
  - ከቅጣት እርከን 16 ጀምሮ በመነሻውና በመድረሻው መካከል ያለው ፍቅድ ስልጣን (range) የመነሻውን ሃያ በመቶ እንዲሆን ተደርጓል።
  - በየደረጃው ያለው የቅጣት እርከን መነሻ ሲቀመጥ፣ ከቅጣት እርከኑ ዝቅ ብሎ ከነበረው የቅጣት እርከን መሀል/ በተለይም ከእርከን 16 ጀምሮ አማካይን መነሻ በማድረግ የቅጣት መነሻና መድረሻው ተወስኗል። የቀድሞው እርከን አማካይ የቀጣዩ እርከን መነሻ ይሆናል።
  - በወንጀል ህጉ ቅጣቱ ከመነሻው እንደሚጀምር የተቀመጠ ስለሆነ፣ ለስሌቱ እንዲቀል የዝቅተኛው የቅጣት እርከን አማካዩ ብዙውን ጊዜ በወንጀሉ ከተቀመጡት መነሻዎች (1 አመት፣ 3 አመት፣ 5 አመት፣ 7 አመት፣ 10 አመት፣ 15 አመት) ጋር ያልተራራቀ በሆነ ጊዜ እነዚህ የቅጣት እርከኑ መነሻዎች እንዲሆኑ ተደርገዋል።

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ህጉ ቁጥር 103(1) እስከ 6 ወር የሚደርስ ቀላል እስራት እስከ 6 ወር በሚደርስ የግዴታ ስራ ሊቀየር እንደሚችል ስለሚያስቀምጥ፣ ለዚህ መመሪያ አላማ የአንድ ቀን እስራት ከአንድ ቀን (8 ሰአት) የግዴታ ስራ ጋር ተመጣጣኝ ተደርጎ ተወስዷል፡፡
- ስለሆነም የእስራት ቅጣቱ በማቅለያ ምክንያት የሚቀነስ ከሆነ ተቀንሶ በተደረሰበት የእስራት ቀናት ልክ የግዴታ ስራ እንዲሰራ ሊወሰን በሚችል መልኩ የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡
- በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣት ወደ መቀጮ እንደሚቀየር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179(ረ) የሚደነግግ በመሆኑ ወደ መቀጮ ሲቀየር ስንት ሊሆን እንደሚችል በሚያሳይ መልኩም የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡

## የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ

- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(2) የተደነገጉትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ የወንጀሉን ክብደት ከግምት ባስገባ መልኩ የገንዘብ መቀጮ ጣሪያዎችን የሚያሳይ የቅጣት እርከን ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል፡፡
- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(2) መሰረት የገንዘብ መቀጮን ለመወሰን የወንጀል አድራጊው የገቢ መጠን፣ ሀብቱ ወዘተ ከግምት ገብተው ስለሚወሠን በወንጀል ሕጉ ከተቀመጠው ጠቅላላ የመቀጮ ወለል ሌላ መነሻ የመቀጮ ቅጣት አልተቀመጠም፡፡
- ሆኖም ግን በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ወይም በሌሎች ሕጎች የመቀጮው መነሻ ከፍ ብሎ ተደንግጎ በሚገኝበት ጊዜ በልዩ ክፍሉ ወይም በልዩ ሕጎቹ ከተመለከተው ዝቅተኛ መቀጮ ሳያንስ መነሻ መቀጮው የሚወሰን እንደሆነ ተደንግጓል፡፡
- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሠረት ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ የተፈጸመ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በመቀጮ ቅጣት እርከን የተቀመጠውን ጣሪያ በአስር እጥፍ በማሳደግ በወንጀል ሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ የመቀጮውን መጠን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

# ...የቀጠለ

- የገንዘብ መቀጮ ሰንጠረዥን አስመልክቶ በተመሳሳይ ይነሱ ከነበሩ ሃሳቦች መካከል አብዛኞቹ ተቀባይነት አግኝተው እንዲካተቱ ተደርል፤ ከእነዚህ መካከል፡-
  - ➢ በተለይ በመመሪያ ቁጥር **1/2002** የገንዘብ መቀጮ ሰንጠረዥ ታሳቢ ተደርጎ የተሰራው በወንጀል ሕጉ ውስጥ ያለዉ የገንዘብ መቀጮ ጣሪያ ብር **500,000** ነበር፡፡
  - ➢ ነገር ግን ከዚህ በላይ መቀጮ የሚጥሉ ሌሎች ልዩ ሕጎችን ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ነበር፡፡
  - ➢ በዚህም መሠረት በልዩ ሕጎች የተደነገገው የመቀጮ ጣሪያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ **90(1)** ከተደነገገው የመቀጮ ጣሪያ በላይ ከሆነ በልዩ ሕጎች ላይ የተቀመጠውን ጣሪያ መሠረት በማድረግ መቀጮው ሊሰላ እንደሚባ በመመሪያ ቁጥር **2/2005** በግልፅ ተቀምጧል፡፡

# ...የቀጠለ

- መቀጮው ወደ ግዴታ ስራ የሚለወጥ በሆነ ጊዜ የወንጀል አድረጊው የቀን ገቢን መሠረት በማድረግ የቀን ገቢውን አንድ ሶስተኛ በመክፈል በምን ያህል ጊዜ መቀጮውን ከፍሎ ሊጨርስ እንደሚችል ታሳቢ ባደረገ መልኩ የግዴታ ሥራው የሚቆይበት ጊዜ ይወሰናል፡፡
- ይሁንና ጊዜው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 96 ከተመለከተው 2 አመት አይበልጥም፡፡

## ደረጃ የወጣላቸዉ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች

- መመሪያ ቁጥር 1/2002 ጨምሮ እስከአሁን ድረስ ራሳቸዉን ችለዉ ደረጃ የወጣላቸዉ ድንጋጌዎች 36 ናቸዉ፡፡
- ነገር ግን ህጉ በሚደነግገዉ አግባቡ ከሌሎች ጋር ተቀናጅተዉ የተዘጋጁት ከተጨመሩ ቁጥሩ ከፍ ይላል፡፡
- እነዚህ ድንጋጌዎች ፡-
  - 241 የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት መንካት
  - 257 መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የመሰናዳት ተግባር
  - 258 ከባድ ሁኔታዎች
  - 259 ተጨማሪ ቅጣቶችና የጥንቃቄ ርምጃዎች
  - 356 የሀሰት ገንዘብ፣ የግደታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን መስራት፣

# ...የቀጠለ

- **357** ወደ ሀሰተኛነት  መለወጥ
- **358** ዋጋዉን ዝቅ ማድረግ
- **359** ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማቅረብ
- **361** ማዘዋወር
- **407** በስልጣን ያለአግባብ መገልገል
- **539** ከባድ የሰዉ ግድያ
- **540** ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ
- **541** ቀላል የሆነ የሰዉ ግድያ
- **543** በቸልተኝነት ሰዉ መግደል
- **555** ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት
- **556** ታስቦ የሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት

# …የቀጠለ

- **557** የቅጣት ማቅለያዎች
- **558** ከጥፋተኛዉ ሃሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት
- **559** በቸልተኝነት የሚፈፀሙ የአካል ጉዳቶች
- **560** የእጅ እልፊት
- **598** በህገወጥ መንገድ ኢትዮጵያንን ለስራ ወደ ዉጭ አገር መላክ
- **620** አስገድዶ መድፈር
- **621** አንድን ወንድ አስገድዶ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈፅም ማድረግ
- **622** በንፅህና ክብር ላይ የሚፈፀም የሀይል ድርጊት
- **623** አዕምሯቸዉን በሳቱ….ሰዎች ላይ የሚፈፀም የክብረ ንፅ ህና ድፍረት በደል
- **624** በሆስፒታል በተኙ…ሰዎች ላይ የሚፈፀም የክብረ ንፅህና ድፍረት በደል
- **625** አንድት ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነትዋን ምክንያት በማድረግ የሚፈፀም ድርጊት

# ...የቀጠለ

- **626** ዕድሜአቸዉ አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸዉ ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል
- **627** በህፃናት ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል
- **628** ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች
- **665** ስርቆት
- **669** ከባድ ስርቆት
- **670** ዉንብድና
- **671** ከባድ ዉንብድና
- **692** አታላይነት
- **693** የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቸክ ማዉጣት የሚሉት ናቸው።

## 1. በመንግስት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

### የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 241 እና 257)

- በአገር ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች በኢፌደሪ የወንጀል ሕግ ውስጥ ከአንቀጽ 238-260 ተደንግገው የሚገኙ ናቸው፡፡
- እነዚህ ወንጀሎች በሁለት ክፍሎች የተከፈሉ ናቸዉ፡፡
  - ➢ የመጀመሪያው ክፍል በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትና በአገር የውስጥ ደህንነት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎችን የሚመለከት ሲሆን
  - ➢ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በመንግሥት የውጭ ደህንነትና በመከላከያ ኃይል ላይ የሚደረጉ ወንጀሎችን ይመለከታል፡፡
  - ➢ ለሁሉም ድንጋጌዎች በሂደት ዝርዝር ጥናት እየተደረገ ደረጃ ይወጣል ተብሎ የሚጠበቅ ቢሆንም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ፍርድ ቤት ከሚቀርቡ ጉዳዮች አኳያ ሲታይ የበለጠ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል ተብሎ በተወሰነዉ መሰረት ደረጃ የተዘጋጀላቸው አንቀጽ 241 እና 257 ብቻ ናቸው፡፡

# ...የቀጠለ

- አንቀጽ **241** የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀልን የሚደነግግ ነው፡፡
- በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንም ሰው
  - ➢ በኃይል ወይም ሌላ ማናቸው ሕገ-መንግሥቱን በሚፃረር መንገድ፣
  - ➢ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር የአገሪቱን ሕዝቦች አንድነት እንዲፈርስ ወይም
  - ➢ ፌዴሬሽኑ እንዲከፋፈል፣ ወይም ከፌደሬሽኑ ግዛት ወይም ሕዝብ ከፊሉ እንዲገነጠል የሚያደርግ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ ከአስር እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት ይቀጣል፡፡

# ...የቀጠለ

- ለአንቀጽ 241 ደረጃዎች የተዘጋጁት፡-
  - ➢ ጥፋተኛው ወንጀል ለመፈፀም የተደራጀ ቡድን አባል መሆን ያለመሆኑን፣
  - ➢ በወንጀሉ የደረሰው የጉዳት መጠን፣
  - ➢ የጥፋተኛው የስልጣን ደረጃ
  - ➢ እንዲሁም በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም የሚሉትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ ነው፡፡
- በዚህ መሠረት አንቀጽ 241 ከአንቀጽ 259 እና 258 ጋር ተሳስሮ 10 ደረጃዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡
  - ➢ ከደረጃ 1-6 አንቀጽ 241 ራሱን ችሎ የቀጠለ ሲሆን
  - ➢ ከደረጃ 7-9 ከወንጀሉ ሕግ አንቀጽ 259
  - ➢ እንዲሁም ደረጃ 10 ላይ አንቀጽ 258 ጋር በማጣመር ደረጃ ተዘጋጅቶለታል፡፡

# …የቀጠለ

- አንቀጽ **259** ለጠቅላላ ምዕራፍ የሚያገለግል ነው፡፡
  - በምዕራፉ ውስጥ በጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ማናቸውም ወንጀል የተፈፀመ በተሾመ ወይም የመሪነት ሥልጣን በተሰጠው ሰው ወይም የግል ጥቅም ለማግኘት በመፈለግ እንደሆነ በተጨማሪነት እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ የሚደርስ መቀጮ ሊወሰንበት ይችላል፡፡
- አንቀጽ **258** ደግሞ ከባድ ሁኔታዎችን የሚዘረዝር ነው፡፡
  - በዚህ ድንጋጌ ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው በተገኙ ጊዜ ቅጣቱ እስከ ሞት ቅጣት ሊደርስ ስለሚችል አንቀጽ **241** ከዚህ ድንጋጌ ጋር ሲጣመር የመነሻ ቅጣት እርከኑ **39** ላይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

# …የቀጠለ

- በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ ለተባለ ሰው ቅጣት ስናሰላ፣
  - ➢ ቀላል ጉዳት በማለት የምንይዝለት በንብረት ላይ እስከ ብር 25,000 ጉዳት ያደረሰ ወይም በሰው ላይ ቀላይ የአካል ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡
  - ➢ መካከለኛ ጉዳት በማለት የምንይዝለት በንብረት ላይ ከብር 25,001 እስከ 50,000 ጉዳት ያደረሰ ወይም በሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያስከተለ ከሆነ ነው፡፡
  - ➢ ከባድ ጉዳት በማለት የምንይዝለት ደግሞ በንብረት ላይ ከብር 50,000 በላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ ወይም ድርጊቱ በሰው ላይ ሞት ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡
- ጥፋተኛው በወንጀል ድርጊቱ በአንድ ጊዜ በገንዘብ ወይም በንብረት ላይ እና በሰው አካል ወይም ህይወት ላይ ጉዳት አድርሶ በገንዘብ ወይም በንብረት ላይ ያስከተለው ጉዳት መጠን እና በሰው አካል ወይም ህይወት ላይ ያስከተለው የጉዳት መጠን የሚገኝበት ደረጃ የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ለመወሰን ከሁለቱ ደረጃ የበለጠ ወይም ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትለውን የጉዳት መጠን መሠረት አድርጎ ቅጣት ይወስናል፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 241 ስር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ከአስር አመት እስከ ሃያ አመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊቀጣ እንደሚችል በድንጋጌው የተመለከተ ሲሆን፣ በተጨማሪነት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 259 መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ሊደርስ የሚችል መቀጮ ሊያስከትል የሚችል ወንጀል በመሆኑ ከደረጃ ሰባት አንስቶ ላሉት የወንጀሉ ደረጃዎች ነጻነትን ከሚያሳጡ የቅጣቶች እርከን ጎን ለጎን የገንዘብ መቀጮ እርከኖች እንዲታከሉ ተደርጓል፡፡
- ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 241 ስር የሞት ቅጣትን በሚወስንበት ጊዜ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 258 መስፈርቶች በተጨማሪ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 117 ድንጋጌዎችን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት ወንጀል እንዲደረግ መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 257)

- አንቀጽ 257 ደግሞ መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የመሰናዳት ተግባርን የሚመለከት ሲሆን ድርጊቱን በህግ ላይ በተዘረዘሩት መንገዶች የፈፀመው ሰው በቀላል እሥራት ወይም አድራጎቱ ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ በተለይ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡
- በመመሪያው ዝግጅት ወቅት ቡድኑ የወሰደው አቋም ንዑስ ድንጋጌዎች የተቀመጡበትን ቅድመ ተከተል መሠረት በማደረግ ደረጃው ቢዘጋጅ ተገቢነት ያለው መሆኑን ነው፡፡
- በዚህ መሠረት

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 257 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ቅጣት ለመወሠን ከንዑስ ፊደል <<ሀ>> እስከ <<ሠ>> ያሉት ድንጋጌዎች የያዟቸው የማቋቋሚያ ነጥቦች፡-
  - ወንጀሉ ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ ከባድነት፣
  - የጥፋተኛው የሥልጣን ደረጃ፣
  - እንዲሁም በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም የሚሉት መስፈርቶች በመሆኑ እነዚህን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ድንጋጌው እራሱን ችሎ 6 ደረጃዎች እንዲሁም ከአንቀጽ 259 ጋር በመጣመር ተጨማሪ 2 ደረጃዎች በጠቅላላ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ 8 የወንጀል ደረጃዎች እንዲኖሩት ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

# ...የቀጠለ

- ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 257 ከወጡት ደረጃዎች መካከል ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 5 ያሉት በወንጀል ድንጋጌው ስር ከንዑስ ፊደል <<ሀ>> እስከ <<ሠ>> በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ አምስት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- የወንጀሉ ደረጃ 6 እና ደረጃ 8 ወንጀሉ ሊያስከትል ይችል የነበረውን አደጋ ከፍተኛነት መሠረት ያደረጉ ሲሆን በሁለቱም ደረጃዎች የአደጋውን ክብደት ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ እያየ ምክንያቱን በግልጽ በማስፈር ሊወስን ይችላል፡፡
- ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በደረጃ 7 የተመለከቱትን የሥልጣንና የጥቅም መስፈርቶች መሟላታቸውን እንደነገሩ ሁኔታ እያየ ምክንያቱን በግልጽ በማስፈር የሚወስን ይሆናል፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 257 ስር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ፡-
  - በቀላል እስራት፤ ወይም
  - ይህ አድራጎት ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ በተለይ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ሊቀጣ እንደሚችል በድንጋጌው የተመለከተ ሲሆን፣
  - በተጨማሪነት የአንቀጽ 259 መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ሊደርስ የሚችል መቀጮ ሊያስከትል የሚችል ወንጀል በመሆኑ ከደረጃ 7 አንስቶ ላሉት የወንጀሉ ደረጃዎች ነጻነትን ከሚያሳጡ የቅጣቶች እርከን ጎን ለጎን የገንዘብ መቀጮ እርከኖች እንዲታከሉ ተደርጓል፡፡

## የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን መስራት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 356-362)

- የወንጀል ሕጋችን ከያዛቸውና በመመሪያ ቁጥር 1/2002 የወንጀል ደረጃ ካልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል
  - በታወቁ ገንዘቦች፣
  - የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣
  - ማህተሞች፣
  - ቴምብሮች ወይም
  - መሳሪያዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚመለከተው ርዕስ ስር ከአንቀፅ 355 እስከ 362 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
- ከአንቀጽ 356 – 361 ለተዘረዘሩ ድንጋጌዎች ዝርዝር ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡ የድንጋጌዎቹን ደረጃዎች ለማዘጋጀት እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች ሁሉ ዝርዝር ሙያዊ ጥናት ተካሂዷል፡፡

# ...የቀጠለ

- በጥናቱም በተቻለ መጠን፡-
  - ከገንዘዝብ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ሌሎች አዋጆችን፣
  - በጉዳዩ ላይ በፍ/ቤቶቻች ያሉ ልምዶችን እና
  - አግባብነት ያላቸው የውጭ አገር ተመክሮዎችን ለመዳሰስ ጥረት ተደርል፡፡
- በርዕሱ ውስጥ ከተካተቱ ድንጋጌዎች መካከል አንቀጽ 362 ራሱን ችሎ ወንጀልን የሚያቋቁም ሣይሆን ከአንቀጽ 356-361 ያሉትን ወንጀሎች የሚመለከት የገንዘብ መጠን አነስተኛ ግምት የሚሰጠው በመሆኑ ወንጀሉ ቀላል በሚሆንበትን ጊዜ ቅጣቱም ቀላል እሥራት ሊሆን እንደሚገባ የሚደነግግ ነው፡፡
- ይሁን እንጂ የንዘቡ መጠን አነስተኛ ነው የሚባለው ምን ያህል ሲሆን ነው? የሚለው ግልጽ ባለመሆኑ በመመሪያው ምላሽ ሊያገኝ የሚገባ በመሆኑ እስከ ብር 1000 /አንድ ሺ/ ግምት ያላቸው ወንጀሎች አነስተኛ ግምት ያላቸው ተደርገው ቢወሰዱ ተገቢ እንዲሆን ታምኖበታል፡፡

# ...የቀጠለ

- በአጠቃላይ እንደየድንጋጌዎቹ ባሕሪ ራሳቸውን ችለዉ የሚቆሙትን በራሳቸው የሚጣመሩበትን ዳግም በማጣመር ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በወንጀል ሕግ ከአንቀጽ 356-362 ቅጣት ለመወሰን በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ጥቅም ግምትን መሠረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ፡-

➢ ወንጀሉ በቀላል ሁኔታ ከተደረገ ተፈጻሚነት ካለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 362 ጋር መጣመር ለሚገባቸው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ለእያንዳንዳቸው አምስት፣

➢ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 356 ዘጠኝ፣

➢ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 357 ዘጠኝ፣

➢ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 358 ዘጠኝ፣

➢ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 359 ዘጠኝ፣

➢ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/1/ሀ ዘጠኝ፣

➢ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/1/ለ ዘጠኝ፣

➢ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/2/ሀ አስራ አንድ እና

➢ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/2/ለ ስድስት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# …የቀጠለ

- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361(2)(ሀ) የሚደነግገው ቅጣት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 362 ስር እንደተመለከተው ቀላል እስራት በመሆኑ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361(2)(ለ) የሚደነግገው ቅጣት የገንዘብ መቀጮ በመሆኑ ሁለቱን ድንጋጌዎች ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 362 ጋር ማጣመር ሳያስፈልግ ራሳቸውን ችለው የወንጀል ደረጃዎች እንዲዘጋጅላቸው ተደርጓል፡፡

## በመንግሥት ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

- በዚህ ርዕስ ሥር ከሚገኙት በርካታ ድንጋጌዎች መካከል በመመሪያ ቁጥር 1/2002 ቅድሚያ ተሰጥቶት ደረጃ የወጣለት አንቀጽ 407 መሆኑ ይታወሳል፡፡
- በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያም ቢሆን በዚህ ርዕስ ሥር ለሚገኙት ሌሎች ድንጋጌዎች ደረጃዎች አልተዘጋጁም፡፡
- ይሁን እንጂ በአንቀጽ 407 ሥር ላሉት ንዑስ አንቀጾች የተዘጋጁት ደረጃዎች በተግባር ሥራ ላይ ሲውሉ የተለያዩ ችግሮች ማጋጠማቸው ስለታወቀ ሰፊ የማስተካከያ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡
- በአንቀጽ 407 መሠረት ቅጣትን ለመወሰን የሚረዱ ፍሬነገሮች የምናገኘው ከንዑስ ቁጥር 2 ነው፡፡
- እነዚህ ፍሬ ነገሮች፡-
  - የወንጀል ፈጻሚው የስልጣን ደረጃ፣
  - ያገኘው ወይም ሊያገኝ የነበረውን ጥቅም፣
  - ያደረሰው ወይም ሊያደርስ የነበረውን ጉዳትና
  - ወንጀሉ የተፈፀመበትን ዓላማ የሚመለከቱ ናቸው፡፡

# ...የቀጠለ

- ይህ የሚያሳየው በተመሣሣይ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች በስልጣን ደረጃቸው መለያየት ምክንያት፣ በተገኘው ወይም ሊገኝ በታሰበው ጥቅም መጠን፣ በደረሰው ወይም ሊደርስ በነበረው ጉዳት እንዲሁም ወንጀሉን ለመፈፀም በነበራቸው ምክንያት /ዓላማ/ የቅጣቱ መጠን ሊለያይ እንደሚችል ነው፡፡
- በአጠቃላይ በድንጋጌው ሥር ለሚገኙ ንዑስ አንቀጾች ደረጃዎች ሲዘጋጁ ከታዩት ችግሮች መካከል ዋናዋናዎቹ፣

➢ የተወሰኑ ጉዳዮች ከህጉ ጋር የማይሄዱ መሆናቸው፣ለምሣሌ ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ወንጀሉ በከባድ ዓላማ የተፈፀመ እንደሆነ ይቆጠራል የሚለውን መጥቀስ ይቻላል፡፡

➢ የወንጀል ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ ከዋሉት መመዘኛዎች መካከል የተወሰኑት በሕጉ ላይ የሌሉ መሆናቸው፣ ለምሣሌ በችግር የሚለውን መጥቀስ ይቻላል፡፡

➢ በቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያነት ቀርበው ሊመዘኑ የሚገባቸው ጉዳዮች የወንጀል ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ መዋላቸው ወዘተ... ይጠቀሳሉ፡፡

# …የቀጠለ

- ደረጃዎች በድንጋጌው የተቀመጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት አድርገው እንዲዘጋጁ ለማድረግ ጥረት የተደረገ ሲሆን በትርጓሜ አሰጣጥ ላይ የነበሩ ክፍተቶች ላይ እንዲታረሙ ተደርጓል፡፡
- በዚህ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ የመንግሥት ሠራተኞችም ሆኑ ሌሎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ **33** መሠረት ተከሰው ጥፋተኛ መሆናቸው በተረጋገጠ ሰዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት ወጥና ትክክለኛ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዱ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡
- በመጨረሻም፡-
  - ➢ አንቀጽ **407(1)** ስድስት ደረጃዎች፣
  - ➢ አንቀጽ **407(2)** አራት ደረጃዎች  እና
  - ➢ አንቀጽ **407 (3)** ሶስት ደረጃዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡
- ድንጋጌው የገንዘብ መቀጮ ጭምር የሚጥል በመሆኑ የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከንም አብሮ ተዘጋጅቷል፡፡

# …የቀጠለ

- ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡-
  - <ከፍተኛ ሥልጣን> ማለት በተሻሻለው የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/5 ውስጥ የተካተቱት ባለስልጣኖች ያላቸው ሥልጣን ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከፍተተኛ ሥልጣን ማለት፡-
    - የህዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽን ም/ቤት አባል መሆን፣
    - ከሚኒስትር ደረጃ በላይ የፌደራል መንግስት ባለ ሰልጣን መሆን፣
    - ሚኒስትር፣ ሚኒስቴር ደኤታ፣ ምክትል ሚኒስትር፣ ኮሚሽነር፣ ምክትል ኮሚሽነር መሆን፣
    - የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ መሆን፣
    - የብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት አባል መሆን፣
    - ከክልል ቢሮ ኃላፊ በላይ ባለስልጣን መሆን፣
    - የክልል መንግስት ቢሮ ኃላፊ መሆን፣
    - የክል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ መሆን፣
    - የአዲስ አበባና የድሬዳዋ መስተዳድር ም/ቤት አባል መሆን፣
    - ከአዲስ አበባና ከድሬዳዋ መስተዳድር ቢሮ ኃላፊ በላይ ባለ ስልጣን መሆን፣
    - የአዲስ አበባና የድሬዳዋ መስተዳድር ቢሮ ኃላፊ መሆን፣
    - በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የፌደራል፣ የክልል እና የአዲስ አበባና የድሬዳዋ መስተዳድሮች ባለ ስልጣን መሆን ማለት ነው፡፡

# ...የቀጠለ

- <**መካከለኛ ስልጣን**> ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ <ሀ> ውስጥ የማይካተቱ ነገር ግን ውሳኔ የሚወስኑ የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች ማለትም የመምሪያ ኃላፊዎች፣ የሥራ ሂደት መሪዎች፣ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተጠሪ የሆኑ ኃላፊዎች፣ የዞን ኃላፊዎች፣ የወረዳ ኃላፊዎችና በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች መምሪያ ኃላፊዎችንና ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸውን ያካትታል፡፡
- <**ዝቅተኛ ሥልጣን**> ማለት መካከለኛ የስልጣን ሀላፊነት በሚለው ውስጥ የማይካተቱ ዝቅተኛ ስራ መደብ ላይ የሚገኙ የመንግስት ሠራተኞችን ሥልጣን ማለት ነው፡፡
- እነዚህ የሥልጣን ደረጃ ትርጓሜዎች ያሉ ቢሆንም የክልሉ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ማቋቋሚያ አዋጅ ወይም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ውስጥ የተመለከቱ ትርጓሜዎች ካሉ እነዚህ ትርጓሜዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- ጥቅም/ጉዳት ማለት የተገኘን ወይም ሊገኝ የታሰበውን ጥቅም እንዲሁም የደረሰውን ወይም ሊደርስ የታሰበውን ጉዳት የሚያካትት ሆኖ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡-
  - ‹በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት› ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር **500,000.00** (አምስት መቶ ሺህ) በላይ ሲሆን ነው፡፡
  - “ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት” ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር **100,001.00** (አንድ መቶ ሺህ አንድ) እስከ ብር **500,000.00** (አምስት መቶ ሺህ) ሲሆን ነው፡፡
  - ‹መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት› ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር **25,001.00** (ሃያ አምስት ሺህ አንድ) እስከ ብር **100,000.00** (አንድ መቶ ሺህ) ሲሆን ነው፡፡
  - ‹ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት› ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር **1,001.00** (አንድ ሺህ አንድ) እስከ ብር **25,000.00** (ሃያ አምስት ሺህ) ሲሆን ነው፡፡
  - ‹በጣም ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት› ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት እስከ ብር **1,000.00** (አንድ ሺህ) ሲሆን ነው፡፡

# ...የቀጠለ

- **ከባድ ዓላማ፡-** ማለት ጥቅም ወይም መብት ላይ የደረሰን ጉዳት ለመመዘን ከተሰጠው ትርጉም ውጪ በተሻሻለው የፌዴራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀፅ 2(9)(ሀ) እና (ሐ) ስር በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት የተፈፀመ ወንጀል ሲሆን ነው፡፡
- ይህም ማለት፡-
  - ከፍተኛ ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈፀሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀሎች፣
  - በአገር ሉዓላዊነት ፣ ኢኮኖሚ፣ ፀጥታ እና በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች ማለት ነው፡፡
- በተፈጸመው ወንጀል የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት በገንዘብ ገምቶ ለማስቀመጥ የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ምክንያቱን በማስቀመጥ የተገኘውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰውን የጉዳት መጠን ደረጃ ይወስናል፡፡

# …የቀጠለ

- በተፈጸመው ወንጀል የተገኘው ጥቅም እና የደረሰው ጉዳት የሚታወቅ ከሆነ ደረጃውን ለመወሰን ከሁለቱ የሚበልጠው ይወሰዳል፡፡
- የመንግሥት ሠራተኛ ያልሆነ ሰው በወንጀል ህግ አንቀጽ 33 መሠረት ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት እርከኑ የሚወሰነው የመንግሥት ሠራተኛ የሆነው ሠው የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት እርከን በተወሠነበት አግባብ ነው፡፡

## በሰው ሕይወት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539-543)

- በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ደረጃ ከተዘጋጀላቸው ተጨማሪ ድንጋጌዎች መካከል በሰው ሕይወት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ይገኙበታል፡፡
- በዚህ ርእስ ስር ለሚገኙ ሁሉም ድንጋጌዎች ደረጃ ያልተዘጋጀ ቢሆንም በተነፃፃሪ ሲታይ በፍርድ ቤቶች ሰፋ ባለ ሁኔታ ለሚቀርቡ ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት ለማዘጋጀት ተሞክሯል፡፡
- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ **539** ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ቅጣትን ለመወሰን፡-
  - በእያንዳንዱ ድንጋጌ ስር ያሉትን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ነጥቦች፣
  - የነጥቦቹን ተደራርቦ መገኘትና
  - የወንጀሉ ድርጊት አፈፃፀም ከባድ ወይም እጅግ በጣም ከባድ መሆኑን መሠረት በማድረግ ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- በዚህ መሠረት፡-
  - የወንጀል ሕግ አንቀጽ **539(1)** ከፊደል "ሀ" እስከ "ሐ" ለተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ደረጃዎች የተዘጋጁ ሲሆን
  - ለአንቀጽ **539(2)** ደግሞ ቅጣቱ አማራጭ የሌለው በመሆኑ አንድ ደረጃ ብቻ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡
- በድንጌው ውስጥ የተመለከተቱት ፍሬ-ነገሮች ተደራርበው መገኘት ወይም ያለመገኘት የወንጀሉን ድርጊት አፈፃፀም ከባድ ወይም እጅግ ከባድ መሆን አለመሆኑን መሠረት በማደረግ ደረጃዎች የተዘጋጁ ቢሆንም ከፍርድ ቤቶች የሚጠበቁ ተጨማሪ ሥራዎች አሉ፡፡
- ለምሳሌ በድንጋጌው ፊደል ተራ ‘ለ’ እና ‘ሐ’ ሥር ደረጃዎችን ለመለየት ይቻል ዘንድ የወንጀሉ አፈፃፀም እጅግ ከባድ መሆን አለመሆኑን መወሰን ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም በመመሪያው ውስጥ እጅግ ከባድ አፈፃፀም የሚባሉትን ድርጊቶች መዘርዘር አስቸጋሪ በመሆኑ ለፍርድ ቤቶች የተተወ ሥራ ነው፡፡
- የወንጀል አፈፃፀሙ እጅግ ከባድ ወይም ከዚያ መለስ ያለነው ብሎ ለመለየትና ቅጣቱን ለመወሰን ከድንጋጌው በተጨማሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ **117(1)** መስፈርቶችን ታሳቢ በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡

# …የቀጠለ

- ሌላው ደረጃ የተዘጋጀለት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ አንቀጽ **540** ነው፡፡
- ይህ ድንጋጌ እንደ አንቀጽ **539** ከባድ አለመሆኑ እንዲሁም በአንቀጽ **541** የተመለከተውን ያህል ቀላል አለመሆኑ ተገልጿል፡፡
- በመሆኑም ዝርዝር መስፈርቶችን (ፍሬ ነገሮችን) የምናገኘው ከአንቀጽ **539** እና **541** ነው፡፡
- በዚህ መሠረት ለአንቀጽ **540** ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ያገለገሉ መስፈርቶች፡-
  - ➢ የፀቡን ምክንያት፣
  - ➢ የመሣሪያ አጠቃቀም ወይም ዘዴና
  - ➢ የአገዳደሉ ሁኔታ የሚሉት ናቸው፡፡
- እነዚህን መስፈርቶች በመጠቀም ለወንጀል ህግ አንቀጽ **540** ድንጋጌ በወንጀል ሕግ አንቀጽ **539** የተመለከተውን ያህል ከባድ እንዲሁም በአንቀጽ **541** የተመለከተውን ያህል ቀላል አለመሆኑን በመግለጽ ሕግ አውጭው ያስቀመጠውን ቅጣት መሠረት በማድረግ ስድስት ደረጃዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡

# ...የቀጠለ

- ሆናም በወንጀል ህግ አንቀጽ 540 ሥር የሚወድቀው ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539 እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 541 ከሚሸፈኑ ድርጊቶች ውጭ በመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 82(1)(መ) ሥር ያለው የተበዳይ ለድርጊቱ መንስኤ መሆን በጠቅላላ ቅጣት ማቅለያነት የሚያዝ አይሆንም፡፡
- በመመሪያው ውስጥ የመሣሪያ አይነቶችን በመዘርዘር የትኞቹ አደገኛ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ማስቀመጥ ከባድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ምክንያቱም የአንዱ አካባቢ ከሌላው የሚለይ በመሆኑ፣ አደገኛ መሣሪያ ማለት ተተኳሽ ወይም ስለት ብቻ ነው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ በመሆኑ ዳኞች የነገሩት ሁኔታ እያዩ ውሣኔ ሊሰጡ ይገባል የሚለው የተሻለ አማራጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ድንጋጌው የሚያስቀጣ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት በመሆኑ የደረጃ አንድ መነሻ ቅጣት እርከን 21 ላይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

# ...የቀጠለ

- እርከን **21** ከ**5-6** ዓመት የሚያስቀጣ በመሆኑ በዚህ መሠረት መነሻው ይወሰናል፡፡
- ለድንጋጌው የተቀመጠው ከፍተኛ  እርከን **33** ነው፡፡
- ይህ እርከን ከ**14**  ዓመት እስከ አሥራ ስድስት ዓመት ከ**10** ወር የሚደርስ ነው፡፡
- መነሻ ቅጣቱ በዚህ ፍቅድ ሥልጣን ውስጥ ተወስኖ  ማክበጃ ምክንያቶች ካሉ እስከ ጣሪያው ማለትም **20** ዓመት ድረስ ወይም በተመሳሳይ ማቅለያዎች ካሉ በተቀመጠው አሰራር መሠረት ቅጣቱ እስከ ወለሉ ይቀንሳል፡፡
- አንቀጽ **541** ሁለት ንዑስ ድንጋጌዎችን የያዘ ቢሆንም በድንጋጌው ንዑስ "ሀ" ሥር የተመለከተው ቅጣት በሚያጋጥም ጊዜ ፍ/ቤቱ በመሰለው ቅጣትን ሊያቀል እንደሚችል ሕግ አውጭው የደነገገ በመሆኑ ደረጃ ያልተዘጋጀለት ሲሆን ለዚሁ አንቀጽ ንዑስ "ለ" ግን በድንጋጌው ሥር ያሉትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ ሦስት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- ሆኖም ደረጃዎቹን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋሉ ፍሬ ነገሮች በድጋሚ ማቅለያ ሆነው ቅጣትን እንዳያቀሉ ፍ/ቤቱ ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

# ...የቀጠለ

- በመቀጠል ደረጃ የተዘጋጀለት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 543 ነው፡፡
- የቸልተኝነት ወንጀል አፈጻጸም ሙያዊ ግዴታ በሌላቸውና የሙያ ግዴታ ባላቸው ተከሳሾች ሲፈጸም ከኃላፊነት አንፃር የተለያየ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(1) እና (2) በግልጽ ተመልክቷል፡፡
- በሌላ በኩል ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ድንጋጌ በቸልተኝነት ሰው የመግደል ወንጀል በሶስት ደረጃዎች ተከፍሎ መታየት እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

➢ የመጀመሪያው ተራ የቸልተኝነትን ድርጊት የሚመለከትና ወንጀሉ በማንኛውም የሰውን ሕይወት፣ ጤና እና ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ግዴታ የሌለበት ሰው ሲፈጸመው የሚያስቀጣ ድርጊት ነው፡፡

➢ ሁለተኛው የቸልተኝነት ዓይነት የድርጊቱ ፈፃሚ የሌላ ሰውን ሕይወትና ጤንነት ወይም ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት ሰው እንደሆነ ነው፡፡

➢ ሶስተኛው የቸልተኝነት ዓይነት የንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ተከታይ ሲሆን ከተራ እና የሙያ ግዴታ ባላቸው ሰዎች ከሚፈጸም የወንጀል ዓይነት የሚለይበት ምክንያት የወንጀል ድርጊቱ ክብደት ነው፡፡

# …የቀጠለ

- አንድ ሰው በአንድ የቸልተኝነት ድርጊት፡-
- ➢ ሁለትና ከሁለት በላይ ሰዎች የገደለ ከሆነ ወይም
- ➢ ግልጽ ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ ሰው የገደለ ከሆነ፣ ወይም
- ➢ የሚያሰክሩ ወይም የሚያፈዙ ነገሮችን ወይም መጠጦችን በመውሰድ እራሱን ከኃላፊነት ነፃ የሚያወጣ ሁኔታ ውስጥ በመግባት ድርጊቱን የፈፀመ ከሆነ የቅጣቱ መነሻ ከፍ ይላል፡፡
- ፍ/ቤቶች የቸልተኝነት ኃላፊነት ሲወስኑ መሠረት ማድረግ ያለባቸው፡-
- ➢ የአድራጊውን የግል ሁኔታ፣
- ➢ ዕድሜውን፣
- ➢ የኑሮ ሁኔታውን፣
- ➢ የትምህርት ደረጃውን፣
- ➢ ሥራውንና
- ➢ ማሕበራዊ ኑሮውን መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 59 ተመልክቷል፡፡

# ...የቀጠለ

- ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 59 መረዳት እንደሚቻለዉ ቸልተኝነት በሁለት ተከፍሏል፡፡
  - የመጀመሪያዉ 59(ሀ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም በማለት የተፈፀመ መሆኑን የሚመለከት ሲሆን
  - ሁለተኛዉ ደግሞ 59(ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት የወንጀል ድርጊቱ ከተፈፀመ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡
- እነዚህን መመዘኛዎች ለአንቀፅ 543 ደረጃዎችን ለማዘጋጀት መጠቀም እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡
- በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543 መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሲሰጥ እንደ ድርጊቱ አፈፃፀም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 59 ሥር የተቀመጡትን መስፈርቶች በመጠቀም፡-
  - ቸልተኝነቱ የታወቀ (የወ/ህ/አ.59(1)(ሀ)) ወይም
  - ያልታወቀ (የወ/ህ/አ.59(1)(ለ)) መሆኑን መወሰን አለበት፡፡

# ...የቀጠለ

- አንቀጽ **543(1)** ስድስት ደረጃዎች እንዲኖሩት የተደረገ ሲሆን መስፈርት ተደርገው የተወሰዱት፡-

➢ የወንጀል ፈጻሚው የችሎተኝነት ሁኔታ እና

➢ የተጠቀመበት መሳሪያ የሚሉት ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡

- አንቀጽ **543(2)** አራት ደረጃች አሉት፤ መስፈርት የተደረጉትም፡-

➢ የአጥፊው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሟች ለድርጊቱ መፈጸም የነበረውን አስተዋፅዖ

➢ እንዲሁም የወንጀል ፈጻሚው የችሎተኝነት ደረጃ ናቸው፡፡

- ለአንቀጽ **543(3)** ደግሞ ሶስት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፤ መስፈርት የተደረጉት በህጉ የተመለከቱት ፍሬነገሮችም፡-

➢ ጥፋተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ ወይም

➢ ወንጀሉን የፈጸመው ግልጽ ደንብ ወይም መመሪያን ተላልፎ እንደሆነ ወይም

➢ የሚያሰክሩ ወይም የሚያፈዙ ንጥረ ነገሮችን ወይም መድሃኒቶችን በመውሰድ እራሱን ከሀላፊነት ነጻ በሚያወጣ ሁኔታ ውስጥ ካስገባ በሁዋላ ቢሆንም...የሚሉት ናቸው ፡፡

# …የቀጠለ

- በዚህ መሰረት ከተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች ውስጥ በአንድ ድርጊት አንዱ ወይም ሁለቱ ወይም ከሁለት በላይ ፍሬ ነገሮች ሊጣሱ ይችላል፡፡
- በመሆኑም በድንጋጌው ከተመለከቱት፡-
  - አንዱ ከተሟላ ደረጃው ዝቅ እንዲል
  - ሶስትና ከዚያ በላይ ከሆነ ደግሞ መነሻ ቅጣቱ ከፍ ብሎ እርከን **29** ላይ እንዲጀመር ተደርጓል፡፡
- በአጠቃላይ ይህንን ድንጋጌ ተላልፈው ጥፋተኛ የሚባሉ ሰዎች ቁጥር ቀላል ባለመሆኑ ደረጃዎቹን በጥንቃቄ ለማዘጋጀት የተሞከረ ቢሆንም በተግባር ችግሮች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡

## በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (555-560)

- በወንጀል ህጉ ከአንቀጽ 555-560 በመመሪያ ቁጥር 1/2002 ደረጃ ተዘጋጅቶላቸው ተግባራዊ እየተደረጉ እንደነበር ይታወሣል፡፡
- የመመሪያ ቁጥር 2/2005 አንዱ ዓላማ በነባሩ መመሪያ አተገባበር ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በማጥናት የተሻለ አማራጭ ማቅረብ በመሆኑ በእያንዳንዱ ድንጋጌ ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡
- የወንጀል ህጉ አንቀጽ 555 ሦስት ንዑስ ድንጋጌዎችን የያዘ ነው፡፡
- በነባሩ መመሪያ ላይ ከነበሩት ችግሮች፡-
    - አንዱ ደረጃዎችን ለማውጣት ከህጉ ውጭ የሆኑ መስፈርቶችን ማስገባቱ ሲሆን
    - ሌላው ችግር ደግሞ የደረጃ አንድ የቅጣት እርከን ከ7 የሚጀምር ስለነበር ቅጣትን በጣም ያቀለለ ነው የሚል ተደጋጋሚ ጥያቄ መቅረቡ ነው፡፡

# ...የቀጠለ

- በዚሁ መሠረት ለድንጋጌው የተዘጋጁት ስድስት የወንጀል ደረጃዎች በድንጋጌው ውስጥ በተመለከቱት ፍሬነገሮች መሠረት እንዲዘጋጁ የተደረገ ሲሆን ደረጃ አንድም እርከን 7 ሳይሆን 16 ላይ እንዲጀምር ተደርል፡፡
- መነሻው ከፍ ብሎ እንዲቀመጥ የተደረገበት ምክንያት ከባድ የአካል ጉዳት ማድረሳቸው የተረጋገጠባቸው ሰዎች መነሻ ቅጣት ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ማቅለያዎች ሲጨመሩ ፍትህን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ቅጣት ይጣልባቸው እንደነበር በመረጋገጡ ነዉ፡፡
- እርከን 16 ላይ መነሻ ቅጣት ከተያዘ ማቅለያ ምክንያቶች ለምሣሌ ሦስት ቢቀርቡና ተቀባይነት ቢያገኙ ቅጣቱ ከ2 ዓመት ከ3 ወር እስከ 2 ዓመት ከ9 ወር ይሆናል ማለት ነው፡፡
- በአጠቃላይ በአንቀጽ 555 ላይ መሠረታዊ የሚባሉ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- በመቀጠል ከአንቀጽ 555ን፣ 557/1/ን እና 557/2/ን በማጣመር ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
  - የወንጀል ህጉ አንቀጽ 556(1) እርከን ሁለት ላይ የሚያርፍ አንድ ደረጃ እንዲሁም
  - አንቀጽ 556/2/ አራት ደረጃዎች እንዲኖሩት ተደርል፡፡
  - 556/2/ ለብቻዉ አራት ደረጃዎች ያሉት ከመሆኑ በተጨማሪ ከአንቀጽ 557 ጋር በማጣመር አምስት ደረጃዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡
- በአንቀጽ 558 ደረጃዎች ላይም ሰፊ የማሻሻያ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡
- ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በድንጋጌው የተቀመጡትን ፍሬ ነገሮች በጥንቃቄ ለይቶ ከመጠቀም በተጨማሪ እርከኑን በተወሰነ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ጥረት የተደረገ በመሆኑ በተግባር ይታዩ የነበሩ ችግሮች ሊቃለሉ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

# ...የቀጠለ

- በነባሩ መመሪያ ለአንቀጽ 559 እና 560 ተዘጋጅተው የነበሩት የወንጀል ደረጃ መግለጫዎች በተመሣሣይ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል፡፡
- በመሆኑም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ‹ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት›፣ 558 ‹ከጥፋተኛው ሀሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት› እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559 ንዑስ አንቀጽ 2 ‹በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች› በወንጀሉ ምክንያት የሚደርሰው የጉዳት ዓይነት እና መጠን ተመሳሳይ በመሆኑ እነዚህኑ እንደ መስፈርትነት በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፡-
  - ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ስድስት፣
  - ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 558 ስድስት እና
  - ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 559(2) ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅቷል፡፡

# ...የቀጠለ

- **በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀልን በተመለከተ በድንጋጌው የተመለከቱትን ማክበጃዎች ማለትም፡-**
  - **<ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀመበት መሳሪያ>፣**
  - **<የሙያ ግዴታን በመተላለፍ የተጣሰ መሆኑ>፣**
  - **<ጉዳት ከደረሰበት ሰው ተጋላጭነት> አንጻር የተቀመጡት መስፈርቶች ለዚህ መመሪያ ሲባል የቅጣት ማክበጃ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡**
- **በወንጀል ህግ አንቀጽ 556(3) የተመለከቱት የቅጣት ማክበጃዎች ዓይነት ላይ በመመስረት እና ከአንድ በላይ ተደራርበው በሚገኙበት ጊዜ የወንጀል ደረጃውን ከፍ እንዲል በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) አራት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅቷል፡፡**

# ...የቀጠለ

- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 557 ተፈጻሚ የሚሆነው አስቦ ከባድ የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555) ወይም ቀላል የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556) የማድረስ ወንጀል ሲፈጸም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ በመሆኑ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(1) ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 557 ያነሰ ቅጣትን ስለሚደነግግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ
  - ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 እና 557 ሰባት እና
  - ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) እና 557 አምስት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል።
- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(1)፣ 559(1) እና አንቀጽ 560 የያዙት ፍቅድ ሥልጣን ጠባብ በመሆኑ ለእያንዳንዳቸው አንድ የወንጀል ደረጃ ተዘጋጅቷል።

## በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ወደ ውጪ ሀገር መላክ

## (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 598)

- በወ/ሕ/አ **598** ሥር የተመለከተው በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር የመላክ ወንጀል የሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተግባር አካል ነው፡፡
- ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በሀገር ደረጃ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ሊፈጸም ይችላል፡፡
- የወ/ሕ/አ **598** የሚመለከተው የኢትዮጵያን ድንበር በማቋረጥ የሚፈጸመውን አለም አቀፍ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን ነው፡፡
- የወንጀል ህጉ አንቀጽ **598**ን በመጣስ ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሆኑና ችግሩ በዜጎቻችን ላይ ሰፊ ችግር እያስከተለ በመሆኑ ምክንያት ቅድሚያ ተሰጥቶት ደረጃ ሊዘጋጅለት እንደሚገባ በመታመኑ በጉዳዩ ዙሪያ ዝርዝር ጥናት ተካሂዷል፡፡
- ደረጃዎችን ለማዘጋጀት በዚሁ ድንጋጌ ስር የመለከቱት የወንጀሉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችና በህግ አዉጭዉ በፀደቁት ዓለምአቀፍ ስምምነቶች የተጠቀሱትን ጭምር በአግባቡ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ህጉ አንቀጽ **598/1/** ስር በማናቸውም ሌላ ህገ-ወጥ መንገድ... የሚለው ሀረግ ግልጽ ባይሆንም አጥፊዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ መንገዶች ምን እንደሆኑ ከተጠቀሰው ፕሮቶኮል ላይ ምልመላና የተጠቀሙበት ዘዴና የብዝበዛ ዓላማ ወዘተ ... ከሚሉት መረዳት ይቻላል፡፡
- ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖር መለክ ብቻውን ወንጀሉን ለማቋቋም በቂ ቢሆንም የላኩ ሰዎች በሙሉ ተመሣሣይ የቅጣት መጠን ይቀጣሉ ማለት አይቻልም፡፡
- በአንቀጽ **598** ስር ለተቀመጡት ሦስት ንዑሳን ድንጋጌዎች ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ መስፈርቶቹም፡-

➢ በህገ ወጥ መንገድ መለክ

➢ አጥፊዎች ያገኙት ጥቅም

➢ ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎችና

➢ የደረሰውን ጉዳት

➢ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች /የግል ተበዳዮች/ ብዛት ጭምር የሚመለከቱ ናቸው፡፡

# ...የቀጠለ

- ሁሉንም መስፈርቶች በቀጥታ በድንጋጌው ውስጥ ማግኘት ባንችልም ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የአገሪቱን ህጎች ጭምር በመመርመር ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ከመረጃዉ መገንዘብ እንችላለን፡፡
- በዚህ መሰረት ለድንጋጌዉ ዝርዝር ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- ደረጃዎቹ የህግ አዉጭዉን ሃሳብ በሚያሟላ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ከዳኞች የሚጠበቅ ሃለፊነት ነዉ፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ **598(1)** እና **(3)** ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጪ ሀገር በመላክ ወንጀል ጥፋተኝነታቸው በፍ/ቤት ለሚረጋገጠባቸው አጥፊዎች፡-
  - ያገኙት ጥቅም እና
  - ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀሟቸው መንገዶች ታሳቢ ተደርገው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ **5** የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598(1-3) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት ለሚረጋገጥባቸው አጥፊዎች የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ብቻ ሆነው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598(2) ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በመውሰድ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 598(1) የወንጀል ደረጃ ለማውጣት ካገለገሉት መለኪያዎች ጋር በማጣመር ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598(3) መሠረት በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ወደ ውጪ ሀገር የመላክ ወንጀል ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ወንዶች ኢትዮጵያውያንንም ስለሚያካትት ለሁለቱም ጾታዎች ተመሳሳይ ደረጃ እና እርከን ተዘጋጅቷል፡፡
- ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 598 ድንጋጌዎች ደረጃ እና እርከን አወጣጥ የዋሉት መስፈርቶች የተወሰዱት በአዋጅ ቁጥር 737/2004 ከጸደቀው ሕገ ወጥ የሰዎች በተለይም የሴቶችና የህጻናት ዝውውርን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የወንጀሉን ፈጻሚዎች ለመቅጣት ከወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፕሮቶኮል ነው፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ደረጃ መግለጫው ላይ የተበዳዮች (የተጐጂዎች) ቁጥር እና በወንጀል ድርጊቱ ላይ የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚወድቁ በሆነ ጊዜ መነሻ ቅጣት ከፍ ባለ ደረጃ ላይ የሚገኝ ይሆናል፡፡

## በግብረ ሥጋ ነጻነትና ንፅህና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620-628)

- አስገድዶ መድፈር በተጎጂ ላይ አካላዊ እና ስነ ልቦናዊ ጉዳት የሚያስከትል ወንጀል ነው፡፡
- ለሰብአዊ መብት ጥበቃን ከሚሰጡት ሁሉ አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ ዓለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት እና ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊና ባህላዊ መብቶች ስምምነት ሰነድን ከመሳሰሉት ባሻገር ሴቶችን በተለይ የሚመለከቱ አለም አቀፍ ስምምነቶች አሉ፡፡
- ከእነዚህም ውስጥ፡-
  - በሴቶች ላይ የሚፈጸም ማንኛውንም አድልዖ ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት እና
  - በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የኃይል ተግባራትን ለማስወገድ የወጣ ስምምነት መግለጫ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

# ...የቀጠለ

- በሀገር አቀፍ ደረጃም ሕገ መንግስቱ በአጠቃላይ ለማንኛውም ሠው እና በተለይ ለሴቶች ጥበቃን ይሰጣል፡፡
- ሕገ መንግስቱን ተከትሎ ከወጡት ሕጎች ውስጥ የወንጀል ሕጉ ተጠቃሽ ነው፡፡
- በመሆኑም የሚወሰኑ ቅጣቶች ወጥነትንና ትክክለኛነትን ያረጋገጡ እና አስተማሪ እንዲሆኑ በማሰብ ለእነዚህ ወንጀሎች ቅድሚያ ተሰጥቶ እንዲጠኑና ረቂቅ የቅጣት መመሪያ እንዲዘጋጅላቸው ተደርጓል፡፡
- በዚህ ርዕስ ስር የወንጀል ደረጃ የተዘጋጀላቸው ድንጋጌዎች ከአንቀፅ **620-628** ተዘርዝረው የሚገኙት ናቸው፡፡
- እነዚህ ድንጋጌዎች ከአሁን በፊት በነበረው መመሪያ ያልነበሩ በመሆኑ በአፈጻጸም ችግር አያጋጥምም ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡

# …የቀጠለ

- ደረጃዎቹን በጥንቃቄ ለመስራት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ክፍተቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡
- ስለዚህ በተመደበው አግባብ የወንጀል ህጉን መሠረት ያደረገ ቅጣት በመወሰን የዜጎችን መብት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ **621** ስር ለተደነገገው ሴቶች በወንዶች ላይ ለሚፈጽሙት አስገድዶ መድፈር፡-
  - የወንጀሉን አፈጻጸም እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ **628** ስር የተመለከቱትን የማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ሕግ አንቀጽ **622** ስር ለተመለከተው በንጽህና ክብር ላይ የሚፈጸም የሀይል ድርጊት፡-
  - የወንጀሉን አፈጻጸም እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ **628** ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ **623** ስር ለተመለከተው አዕምሯቸውን በሳቱ ወይም የአዕምሮ ደካማ በሆኑ ወይም ለመቃወም በማይችሉ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽህና ድፍረት በደል፡-
  - የወንጀሉን ዓይነት እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ **628** ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ሕግ አንቀጽ **624** ስር ለተመለከተው ሆስፒታል ውስጥ በተኙ፣ በተጋዙ ወይም በታሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽህና ድፍረት በደል፡-
  - የወንጀሉን ዓይነት እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ **628** ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ **625** ስር ለተመለከተው አንድ ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነቷን ምክንያት በማድረግ ለሚፈጸም ድርጊት፡-
  - የወንጀሉን ዓይነት እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ **628** ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(1) ስር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል፡-
  - የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(4)(ሀ) እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(2) ስር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል፡-
  - የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(4)(ለ) እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(3) ስር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል፡-
  - የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(4)(ሐ) እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(1) ስር ለተመለከተው በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል፡-
  - የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(4)(ሀ) ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አራት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# …የቀጠለ

- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(2) ስር ለተመለከተው በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል፡-
  - የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(4)(ለ) እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(3) ስር ለተመለከተው በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል፡-
  - የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(4)(ሐ) እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(5) ማክበጃ ምክንያቶች ተሟልተው ከተገኙ የሚጣለውን የቅጣት ዓይነት ሕጉ እራሱ ወስኖ ስላስቀመጠው አንድ የወንጀል ደረጃ ብቻ ተዘጋጅቷል፡፡

## የስርቆት ወንጀሎች (665 እና 669)

- በዚህ ርዕስ ስር ደረጃ የወጣላቸው ድንጋጌዎች አንቀጽ 665 እና 669 ሲሆኑ እነዚህ ድንጋጌዎች በመመሪያ ቁጥር 1/2002 የነበሩና በአፈጻጸም ረገድ የጎላ ችግር አስከትለዋል ተብለዉ ሲጠቀሱ እንደነበር ይታወሳል፡፡
- በተለይ በአንቀጽ 665 አፈጻጸም ላይ ሰፊ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የተነሱ በመሆናቸው በማሻሻያው ወቅት ሰፊ ጊዜ ተወስዶ ውይይት ተካሂዷል፡፡
- በነባሩ መመሪያ ውስጥ ከተነሱት ችግሮች የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፡-
  - እስከ ብር 100 ያለው በደንብ መተላለፍ መታየት አለበት ተብሎ የመጀመሪያው ደረጃ ከብር 100-1000 ብሎ መጀመሩ ህጉን የሚጥስ ነው፤
  - ደረጃው የተዘጋጀው የተሰረቀ ገንዘብ መጠንን /ግምትን/ መሠረት በማድረግ በመሆኑ የወንጀል ሀሳብን አይቀጣም፤
  - ደረጃው ዝቅ ብሎ የጀመረ በመሆኑና ወንጀል ፈጻሚዎችም ይህንኑ በመገንዘብ የማቃለያ ምክንያቶችን እየደረደሩ ቅጣት መወሰን አልተቻለም፤
  - በአጠቃላይ መመሪያው አጥፊዎችን የሚያርም አይደለም የሚል ሰፊ ትችት ነበር፡፡

# ...የቀጠለ

- የገንዘብ መጠን ብቻ ከታየ ሃሳብን ለመቅጣት አስቸጋሪ ይሆናል የሚለዉን ችግር ለመፍታት እንዲቻል ፍ/ቤቱ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚውን ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ክፍል **(Intention)** ለመቅጣት በቂ አይደለም ብሎ ሲያምን ምክንያቱን በመግለጽ ሁለት እርከን በማሳደግ የቅጣቱን መነሻ ሊወስን እንደሚችል በመመሪያው አንቀጽ **16(3)(ሀ)** ስር ተደንግጓል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ እስከ ብር **100** ያለው በደንብ መተላለፍ ይታያል መባሉ አግባብ ባለመሆኑ እንዲታረም ከመደረጉም በላይ ለአንቀጽ **665** መነሻ ቅጣት እርከን ሁለት ሣይሆን ስድስት እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- በአጠቃላይ የስርቆት ወንጀል ከትንሽ እስከ ትልቅ ሊባል በሚችል ደረጃ በህብረተሰቡ ውስጥ በየዕለቱ የሚያጋጥም ነው፡፡
- ስለዚህ በመመሪያ ምክንያት ያልተገባ ውሣኔ እንዳይሰጥ ማስተካከያ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

# ...የቀጠለ

- ለቀላል ስርቆት ወንጀል በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበውን ገንዘብ ወይም ንብረት ጥቅም ግምት መሠረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስምንት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- ልዩ ሁኔታዎች፡-
  - ➢ ድንጋጌውን አስመልክቶ የተቀመጠው የመቀጮ ሠንጠረዥ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቱ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚውን ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ክፍል **(intention)** ለመቅጣት በቂ አይደለም ብሎ ሲያምን ምክንያቱን በመግለፅ ሁለት እርከን በማሳደግ የቅጣቱን መነሻ ሊወስን ይችላል፡፡
  - ➢ ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በተሰረቀበት ሀብት ወይም ንብረት ምክንያት የዕለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ ፍ/ቤቱ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደላይ ከፍ አድርጎ መወሰን ይችላል፡፡
  - ➢ የተሰረቀው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ነገር ወዘተ ከሆነ ፍ/ቤቱ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ደረጃ ወደላይ አሳድጎ መወሰን ይችላል፡፡
  - ➢ ከላይ የተዘረዘሩት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ ፍ/ቤቱ እያንዳንዱ የሚያስጨምረው እርከን ተደምሮ የሚያስገኘው እርከን ድረስ ከፍ አድርጎ ቅጣት መወሰን እንደሚችል ተደንግል፡፡

# ...የቀጠለ

- ለከባድ ስርቆት ወንጀል ለወንጀል ሕግ አንቀጽ **665** የተዘጋጀውን የገንዘብ መጠን መነሻ መሠረት ባደረገ መልኩ እና በድንጋጌው የተመለከቱትን ማክበጃዎች ማለትም፡-
  - ➢ የተሰረቀው እቃ ዓይነት፣
  - ➢ ድርጊቱን የፈጸመው አድራጊ ማንነት፣
  - ➢ የወንጀል አፈጻጸሙን መሠረት ባደረገ መልኩ ዘጠኝ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ **669** ሥር ከተዘረዘሩት ወንጀሉን የሚያከብዱ ምክንያቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው በሚገኙበት ጊዜ የወንጀል ደረጃውና መነሻ ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡
- በወንጀሉ የተገኘውን የጥቅም መጠን መገመት ባልተቻለ ጊዜ ወይም በገንዘብ የሚገመት ካልሆነ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በማስቀመጥ በቅጣት እርከኑ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ባለው ደረጃ እና እርከን መሠረት ሊወስን ይችላል፡፡_

## የውንብድና ወንጀሎች (670 እና 671)

- አንቀጽ 670 እና 671 በነባሩ መመሪያ ደረጃ ተዘጋጅቶላቸው የነበሩ ናቸው፡፡
- ለወንጀል ህግ አንቀጽ 670 እና 671 ድንጋጌዎች ደረጃዎች ሲዘጋጁ ታሣቢ የተደረጉ መመዘኛዎች፡-
  - የተገኘ ወይም ሊገኝ የታሰበውን የገንዘብ ጥቅም ወይም
  - የደረሰ ወይም ሊደርስ የታሰበውን ጉዳት እና
  - የሀይል አጠቃቀሙ የሚሉት ናቸው፡፡
- እነዚህን መመዘኛዎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጁት ደረጃዎች በተግባር ላይ ሲውሉ የጐላ ችግር ስላላጋጠመዉ በአሁኑ መመሪያ የተወሰኑ የደረጃዎች ሽግሽግና ማስተካከያዎችን ብቻ በማድረግ ባሉበት እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡

# ...የቀጠለ

- በዚህም መሰረት፡-
  - ለወንጀል ሕግ አንቀጽ **670** ዘጠኝ፣
  - ለወንጀል ሕግ አንቀጽ **671(1)** ዘጠኝ፣
  - እንዲሁም ለወንጀል ሕግ አንቀጽ **671(2)** ሁለት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- ደረጃዎች ሲዘጋጁም ወንጀለኛው ወንጀሉን ሲፈፅም የማስፈራራትና ኃይል የመጠቀሙ ተግባር የፈጸመው፣
  - መሳሪያ ሳይያዝ በሆነ ጊዜ ................ዝቅተኛ
  - መሳሪያ ተይዞ ከሆነ .......................መካከለኛ
  - የጦር መሳሪያ በመያዝ ከሆነ .......ከፍተኛ በማለት እንደቅደም ተከተላቸው የወንጀል አፈጻጸሙን የሚያከብዱ እንደሚሆኑ ታሳቢ በማድረግ የወንጀል ደረጃዎቹ ተዘጋጅተዋል፡፡

## የማታለል ወንጀሎች (692 እና 693)

- በዚህ ርዕስ ስር ደረጃ የወጣላቸው ድንጋጌዎች አንቀጽ 692 እና 693 እንደነበሩ እናስታውሳለን፡፡
- በማታለል ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች ባጋጠሙ ጊዜ ቅጣቱ እንዴት መወሰን አለበት የሚለውን በዝርዝር ከማስቀመጥ በተጨማሪ በእያንዳንዱ ድንጋጌ ስር የነበሩ ደረጃዎችን በመፈተሽ የተሻሉና ህጉን መሠርት ያደረጉ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡
- የማታለል ወንጀልን (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692) በተመለከተ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበውን የገንዘብ ወይም ንብረት ጥቅም ግምትን መሠረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስምንት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

# ...የቀጠለ

- ልዩ ሁኔታዎች፡-
  - ፍ/ቤቱ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚውን ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ክፍል **(intention)** ለመቅጣት በቂ አይደለም ብሎ ሲያምን ምክንያቱን በመግለፅ ሁለት እርከን በማሳደግ የቅጣቱን መነሻ ሊወስን ይችላል፡፡
  - ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በማታለሉ ተግባር በተወሰደበት ገንዘብ ወይም ንብረት ምክንያት የዕለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ ፍ/ቤቱ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ቅጣት ይወስናል፡፡
  - በማታለሉ ተግባር የተወሰደው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደ ላይ ያድጋል፡፡
  - የተወሰደው ንብረት ለወንጀል ተጎጂው ልዩ ትርጉም ያለው ከሆነና ወንጀል አድራጊውም ይህንን እያወቀ የወሰደው ከሆነ በአንድ እርከን ወደ ላይ ያድጋል፡፡

# ...የቀጠለ

- ከላይ የተዘረዘሩት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ እያንዳንዱ የሚያስጨምረው እርከን ተደምሮ የሚያስገኘው እርከን ድረስ ከፍ ይላል፡፡
- ቢሆንም ግን ፍ/ቤቱ በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ በላይ መወሰን አይችልም፡፡
- የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ የማውጣት ወንጀል (አንቀጽ 693) ቅጣት አጣጣል ላይ ሰፊ ቅሬታዎች ይቀርቡ ነበር፤ በመሆኑም፡-
  - ➢ በአንድ በኩል ቅጣቱ ሲጣል ከተገቢው በላይ እንዳይከብድ
  - ➢ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የወንጀል ድርጊት በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ውስጥ ተጽዕኖ እንዳይፈጥር የሚያስችል አስተማሪ ቅጣት እንዲጣል ማድረግ የህግ አውጭው ፍላጐት ነው፡፡
- ስለዚህ በነባሩ መመሪያ የደረጃ አንድ መነሻ እርከን ሁለት መደረጉ የቅጣት ማቅለያዎችን ግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ ወደ እርከን አምስት ከፍ እንዲል ከመደረጉም በላይ ደረጃዎቹ በማነሳቸው ከትንሽ እስከ ትልቅ የንዘብ መጠን ወንጀሉን የፈፀሙ ሰዎች በአንድ ላይ እየሆኑ የቅጣቱን ፍትሃዊነት ያጓደለ መሆኑ ስለተረጋገጠ ሰፊ ማስተካከያዎች ተደርገዋል፡፡
- በዚህም መሰረት የገንዘቡን መጠን መነሻ በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አሥራ አንድ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

## ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎች የወንጀል ደረጃና የቅጣት መነሻ እርከን አወሳሰን

- ደረጃ የወጣላቸው ድንጋጌዎች ቁጥር ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግም ለምን ለሌሎች ድንጋጌዎች ጭምር ደረጃዎች አይዘጋጁም የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡
- ነገር ግን ስራው በመደበኛነት ሳይሆን ለተወሰነ ጊዜ ኮሚቴ እየተሰየመ የሚሰራው በመሆኑ የተፈለገውን ያህል ርቀት መሄድ አልተቻለም፡፡
- በሌላ በኩል ሁሉንም አንድ ጊዜ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ ልምድን በማዳበር በተከታታይ መስራቱ የተሻለ ነዉ፡፡
- ነገር ግን ሂደቱ አዝጋሚ ሊሆን አይገባም፡፡ ምክንያቶቹ ምንም ይሆኑ ምን ለበርካታ ድንጋጌዎች ገና ደረጃዎቹ ያልተዘጋጀላቸው በመሆኑ ስራው እስኪጠናቀቅ ድረስ ቅጣትን ተቀራራቢ በሆነ መንገድ ለመወሰን የሚረዳ የመፍትሄ አማራጭ መፈለግ ተገቢ ነው፡፡
- ይህንን ታሳቢ በማድረግ በመመሪያ ቁጥር 1/2002 ውስጥ የተካተተው አሰራር የድንጋጌውን የቅጣት መጠን ለአራት በመክፈል ዉጤቱን በዝቅተኛ፣ በመካከለኛና ከፍተኛ በመመደብ ቅጣትን መወሰን ነው፡፡

# …የቀጠለ

- በዚሁ አሰራር ላይ ከሚነሱ ጥያቄዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ
  - የቅጣት መጠኑን ለአራት የመክፈሉ አስፈላጊነት ምንድን ነው?
  - የመጨረሻ እርከን ለቅጣት ማክበጃ ተብሎ የተተወና መነሻ ቅጣት የማይወሰንበት በመሆኑ በተለይ ማክበጃ ምክንያቶች አልተገኙም በማለት የቅጣቱ መጠን ዝቅተኛ እየሆነ ችግር አስከትሏል፤
  - ደረጃውን ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ብሎ ለመወሰን ታሳቢ ማድረግ የሚገባቸው መመዘኛዎች ያልተቀመጡ በመሆኑ የነበረውን የቅጣት መለያየት ማስቀረት አልተቻለም የሚሉት ይገኙበታል፡፡
- እነዚህንና እንደነገሩ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ በሚለያቸው ሌሎች መመዘኛዎች መሰረት ቀላል፣ መካከለኛ ወይም ከባድ በማለት ከተለየ ቀላሉ እርከን አንድ ሲባል መካከለኛና ከባድ የተባሉት ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው እርከን ሁለትና ሶስት ይሆናሉ፡፡

# ...የቀጠለ

- ከአሁን በፊት በነበረው አሰራር እርከን አራት የቅጣት ማክበጃዎች በተገኘ ጊዜ ከፍ በማድረግ ለመወሰን እንዲቻል ታስቦ የተተወ ነበር፡፡
- ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው የማክበጃ ምክንያቶች ባልተገኙ ጊዜ ወይም ቢገኙም በተለይም በአንዳንድ ወንጀሎች ቅጣትን ከፍ ለማድረግ ችግር ሆኖ ሲነሳ ነበር፡፡
- ስለዚህ በአዲሱ መመሪያ  የተፈጸመው ወንጀል እጅግ ከባድ ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ መነሻ ቅጣቱን በእርከን አራት ስር መወሰን እንደሚቻል  ተቀምጧል፡፡
- ከአሁን በፊትም ቢሆንም ፍትህን ለማረጋገጥ ሲባል ፍርድ ቤት ከመመሪያው ወጥቶ  መወሰን እንደሚቻል የተገለጸ ቢሆንም ጉዳዩን  የበለጠ ግልጽ ማድረግ የተሻለ በመሆኑ የተጠቀሰው ሀሳብ እንዲካተት ተደርጓል፡፡
- ይህ አሰራር አሁንም ውስንነቶች ሊኖሩበት የሚችሉ ቢሆንም፡-
- ➢ ቢያንስ በምክንያት ላይ የተመሰረተ ደረጃን በመለየት
- ➢ እንዲሁም የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ዋጋ በግልጽ በማስቀመጥ የሚሰራ በመሆኑ ከነባሩ አሰራር የተሻለ ነው፡፡
- ክፍተቶች ካሉ በመሙላት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ማድረግ የሁላችንም ሀላፊነት ነው፡፡

# ...የቀጠለ

- በመሆኑም በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2005 መሰረት ቅጣት ስንወስን ቀጥሎ ባሉት መርሆዎች መሰረት መሆን ይገባዋል፡፡
- ወንጀሉን የሚደነግገው ድንጋጌ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት ሊያስቀጣ እንደሚችል በደነገገ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ደረጃውን ለማውጣት በቅድሚያ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይወስናል፡፡
- በመቀጠልም ፍርድ ቤቱ በወንጀል ድንጋጌው ከተቀመጠው መስፈርት አንጻር እና የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ታሳቢ ከማድረጉ በፊት ወንጀሉን በክብደቱና በአፈጻጸሙ፡-
  - ቀላል፣
  - መካከለኛ፣
  - ከባድ የወንጀል ደረጃ በማለት ይመድባል፡፡
- ፍርድ ቤቱ ወንጀሉን ቀላል፣ መካከለኛ ወይም ከባድ በማለት ለመመደብ ምክንያቱን በውሳኔ ሰነዱ ላይ ያስቀምጣል፡፡

# …የቀጠለ

- የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን፡-
  - የወንጀሉ አፈጻጸም ሁኔታ
  - የደረሰው ጉዳት ዓይነትና መጠን፣
  - የተገኘው ጥቅም መጠን፣
  - ወንጀሉ ታስቦ የተሰራ መሆን አለመሆኑ፣
  - ወንጀሉ በቸልተኝነት ሲሰራ የሚያስቀጣ ከሆነ ቸልተኝነቱ የታወቀ ወይም ያልታወቀ ቸልተኝነት መሆኑ እንደ መስፈርት ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡
- ፍርድ ቤቱ በእነዚህ መስፈርቶች ብቻ ሳይወሰን ደረጃውን ለመወሰን የሚያስችሉ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ሌሎች መስፈርቶችን ለመጠቀም ይችላል፡፡
- ሆኖም ግን ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች ደረጃውን ለመወሠን እንደመለኪያ (መስፈርት) ሊወሠዱ አይችሉም፡፡

# ...የቀጠለ

- የወንጀል ደረጃው ከተለየ በኋላ ለወንጀል ደረጃው የቅጣት እርከኑን ለመወሰን እንዲቻል በልዩ ክፍሉ ለወንጀሉ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ያለውን ርዝመት ለአራት እኩል በመክፈል፡-

➢ በወንጀል ሕግ ለቅጣቱ መነሻ ተብሎ ከተቀመጠው የቅጣት መጠን የሚጀምረው አንድ አራተኛ መጠን እርከን አንድ ይባላል፡፡

➢ ከመጀመሪያው አንድ አራተኛ ቀጥሎ ያሉት እርከኖች እንደ ቅደም ተከተላቸው እርከን ሁለት፣ እርከን ሶስት፣ እርከን አራት ይባላሉ፡፡

- በመቀጠል፡-

➢ <ቀላል> በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን አንድ ባለው ፍቅድ ሥልጣን (range) ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

➢ <መካከለኛ> በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን ሁለት ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

➢ <ከባድ> በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን ሦስት ባለው ፍቅድ ሥልጣን (range) ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ሆኖም የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት እጅግ ከባድ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ከወሠነ በዚህ ድንጋጌ ሳይወሰን መነሻ ቅጣቱን በእርከን 4 ሥር ሊወስን ይችላል፡፡

# ...የቀጠለ

- በፍርድ ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በቅጣት ሠንጠረዥ እርከኑ ላይ የትኛው እርከን ላይ እንደሚወድቅ በመለየት የቅጣት እርከኑን በሰንጠረዡ መሠረት ይለያል፡፡
- ፍርድ ቤቱ ያስቀመጠው የቅጣት መጠን በቅጣት እርከኑ የቅጣት ሠንጠረዥ ሁለት ተከታታይ እርከኖች ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ፣ በዝቅተኛው እርከን ውስጥ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡
- በዚህ መሠረት ቅጣታቸው የሚወሰን የወንጀል አይነቶች በመቀጮ ብቻ የሚያስቀጡ ወይም በመቀጮ ወይም በእስር የሚያስቀጡ ወይም በመቀጮ እና በእስር የሚያስቀጡ መሆኑ በተደነገገ ጊዜ፣ ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 92(2) መሠረት መቀጮ መጣል የሚያስፈልግ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ወይም ልዩ ክፍል ወይም በሌላ ሕግ የተቀመጠውን ጣሪያ መሠረት በማድረግ፡-
  - <ለከባዱ> በሕጉ እስከተመለከተው ጣሪያ ድረስ፣
  - <መካከለኛ> ለሆነው በሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ አንድ ሶስተኛ በመቀነስ የሚደረስበትን መጠን ጣሪያ በማድረግ፣
  - እንዲሁም <ቀላል> ለሆነው ከጣሪያው በሁለት ሦስተኛ ዝቅ ብሎ በሚደርስበት ጣሪያ ሳይበልጥ መቀጮውን ይወስናል፡፡
- ሆኖም መነሻ የገንዘብ መቀጮ ህግ አውጪው በልዩ የወንጀል ሕግ ድንጋጌው ካስቀመጠው መነሻ ቅጣት በታች ሊወርድ አይችልም፡፡

## የማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶችን ስለማስላት

- በተመሣሣይ ጥፋት ተመሣሣይ በሆነ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ በተባሉ ሰዎች መካከል የቅጣት አይነትና መጠን ልዩነት የሚኖረው በቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ነው፡፡
- የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች፡-
  - የተወሰኑት በቀላሉ ሊረጋገጡ የሚችሉ **(objective)** ሲሆኑ
  - ሌሎች ደግሞ ከጥፋተኛው የግል ሁኔታ (ባሕሪይ) ጋር የሚዛመዱ ስለሆኑ በቀላሉ ለማረጋገጥ የሚያስቸግሩ **(subjective)** ናቸው፡፡
- ለምሣሌ አንድ ወንጀለኛ፡-
  - ተፀፀቶ በደል ላደረሰበት ሰው እርዳታ ማድረጉን፣
  - ጥፋቱን በመገንዘብ ራሱን ለፍትህ አካል ማቅረቡን፣
  - ጉዳት ላደረሰበት ሰው በተቻለ መጠን ካሣ መክፈሉን ወይም
  - ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ በክስ ማመልከቻ ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ማመኑን ወይም አለማመኑን በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

# ...የቀጠለ

- በሌላ በኩል ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው ከፍ ባለ ኃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ ወይም ማህበራዊ እምነት ተነሣስቶ መሆኑ ከተረገገጠ ቅጣቱ ሊቀልለት እንደሚችል ተቀምጧል፡፡
- ነገር ግን ይህንን ማረጋገጥ ቀላል አይደለም፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ድርጊቱን ከፍ ያለ አደጋ የሚያመጣ ነገር የተቃጣብኝ መስሎኝ ወይም ፍርሀት አድሮብኝ የፈፀምኩት በመሆኑ ቅጣቱ ይቅለልልኝ በማለት ሃሳብ ያቀርባል፡፡
- ሆኖም ግን እነዚህንና መሰል ጉዳዮችን ለመመዘን መለኪያው  አጥፊው ሣይሆን ሌላ ምክንያታዊ ሰዉ ነው፡፡
- አጥፊው ያቀረበው ሃሳብ በእርግጥም በምክንያታዊ ሰው እይታ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ ይመዘናል፡፡ ይህ በአግባቡ ካልተመዘነ ውጤቱ ያልተጠበቀ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡

# ...የቀጠለ

- የማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች በአጠቃላይ በሁለት የሚከፈሉ ናቸው፡፡ እነርሱም፡-
    - ➢ በሕጉ ውስጥ በግልፅ ተዘርዝረው የምናገኛቸው እና
    - ➢ በሕጉ ባይዘረዝሩም ዳኞች አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣናቸውን ተጠቅመው ምክንያታቸውን በመጥቀስ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ናቸው፡፡
- ስለዚህ የእነዚህ ምክንያቶች ብዛት ይህን ያህል ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡
- ከዚህ አኳያ አዲሱ መመሪያ ከነባሩ የሚለይባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ሁለት ናቸው ፡፡

    የመጀመሪያው፡-

    - ➢ እንደሚታወቀው በአንድ ንዑስ ድንጋጌ ሥር የሚገኙ ዝርዝር የማቅለያ ወይም የማክበጃ ምክንያቶች እንደ አንድ ተወስደው ቅጣቱ ቢወሰን አሰራሩ ቀላልና ግልጽ ይሆናል በሚል ይኸው ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

# ...የቀጠለ

- ይሁን እንጂ በዚህ ላይ የተነሳው ጥያቄ በአንድ ንዑስ ድንጋጌ ሥር ለምሣሌ በአንቀጽ 84 (ሐ) ከተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮች መካከል አጥፊው ወንጀልን ማድረግ ልማድ አድርጎ መያዙ እና ድርጊቱን ሌሊት ስለመፈፀሙ የተረጋገጠበት ሰዉ እና ከእነዚህ አንዱ ብቻ የተገኘለት እንዴት እኩል ቅጣት ይከብድባቸዋል የሚል ነው፡፡ በማቅለያ ምክንያቶች ተመሣሣይ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ እኩል የቅጣት ቅናሽ ከተደረገም ፍትሃዊ አይደለም የሚል አስተያየት ይቀርባል፡፡
- ስለዚህ በአንድ ንዑስ ድንጋጌ ሥር የተዘረዘሩትን አንድ አንድ ምክንያቶች መወሰዱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ፍትህዊነትን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡና የተደራረቡ ምክንያቶች ካሉ በውሣኔው ላይ ግምት የማይገቡበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በአንድ ፈደል (ንዑስ ድንጋጌ) ሥር የተደረቡ የቅጣት ማቅለያ ወይም ማክበጃ ምክንያቶች መኖራቸው ሲረጋገጥ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በመግለጽ ቅጣቱን ማክበድ ወይም ማቅለል እንደሚቻል በድንጋጌጋው ውስጥ ተካቷል፡፡

# ...የቀጠለ

**ሁለተኛው መሠረታዊ ጉዳይ**

- **የማቅለያና ማክበኛ ምክንያቶች እኩል ዋጋ ሊኖራቸው ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡**
- **በመሆኑም በልዩ ማቅለያና ማክበጃዎች ምክንያቶች እንዲሁም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 179 መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች እኩል ዋጋ እንዲኖራቸዉ ተደርጓል፡፡**

## የቅጣት ማክበጃዎችን ስለ ማስላት

### ጠቅለላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር

- **ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ<ሀ> እስከ <ሠ> በአምስት ንዑሳን ድንጋጌዎች ተዘርዝረው የተመለከቱት ማክበጃ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ማክበጃ ምክንያት በጠቅላላው እንደ አምስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡**
- **ሆኖም በአንዱ ፊደል ስር የተደራረቡ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በተገኙ ጊዜ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በመግለፅ ቅጣቱን እንደ ሁኔታው በማክበድ ሊወስን ይችላል፡፡**
- **ነገር ግን በተደራራቢነት የሚወሰዱ እና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ፊደላት ሥር የሚገኙ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አጠቃላይ ብዛት ከአምስት መብለጥ የለባቸውም፡፡**
- **በእያንዳንዱ ድንጋጌ <ሀ>፣<ለ>፣<ሐ>፣<መ>፣<ሠ> ከተመለከቱት ምክንያቶች**

# ...የቀጠለ

- በእያንዳንዱ ድንጋጌ <ሀ>፣<ለ>፣<ሐ>፣<መ>፣<ሠ> ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሲከብድ የሚደርስበት የቅጣት እርከን ውስጥ ባለው ፍቅድ ስልጣን **(range)** ከዝቅተኛው እስከ ጣሪያው ባለው ውስጥ ቅጣቱ የሚወድቅበትን ይወስናል፡፡
- ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን አንድ እርከን ወደላይ ይጨምራል፡፡
- ስለሆነም በቅጣት ማክበጃዎቹ ቁጥር ልክ የቅጣት እርከኑም እንደዚሁ ያድጋል፡፡
- ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ወይም በሌሎች ልዩ ልዩ የወንጀል ሕጎች ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ ማለፍ አይችልም፡፡

## ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር

- ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ፡-
  - በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 በተመለከተው መሠረት ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣት ወስኖ የሚደመር በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ መሠረት ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ካስቀመጠ በኋላ እነዚህን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመምረጥ እርከኑን ይለያል፡፡
  - በመቀጠልም በወንጀል ሕግ ከተመለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱ ያድጋል፡፡
- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛ ፓራግራፍ እና ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) እንደተመለከተው ቅጣቱ የሚከብድ በሆነ ጊዜ፡-
  - ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ከመነሻው እርከን በሁለት እርከን እንዲያድግ ይደርጋል፡፡
  - በመቀጠልም ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሠረት አድርጎ ይከብዳል፡፡ ይሁንና ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ጣሪያ መብለጥ የለበትም፡፡

# ...የቀጠለ

- ጥፋተኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል የመነሻ ቅጣቱ የሚያርፍበትን እርከን በዚህ መመሪያ መሠረት ከለየ በኋላ ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 188 በተመለከተው መሠረት ከአንድ እርከን ጀምሮ ቅጣቱን ሊያሳድግ ይችላል፡፡
- በመቀጠልም ጠቅለላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳል፡፡
- ነገር ግን በወንጀል ሕጉ ጠቅለላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት ከተቀመጠው ጣሪያ ሊበልጥ አይችልም፡፡

## የቅጣት ማቅለያዎችን ስለ ማስላት

### ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ስለሚኖረው አሰራር

- ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ<ሀ> እስከ <ሠ> በአምስት ንዑሳን ድንጋጌዎች ተዘርዝረው የተመለከቱት ማቅለያ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ማቅለያ ምክንያት በጠቅላላው እንደ አምስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡
- ሆኖም በአንዱ ፊደል ስር የተደራረቡ የቅጣት ማቅለያ ድንጋጌዎች በተገኙ ጊዜ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በመግለጽ ቅጣቱን እንደ ሁኔታው በማቅለል ሊወስን ይችላል፡፡
- ነገር ግን በተደራራቢነት የሚወሰዱ እና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ፊደላት ሥር የሚገኝ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አጠቃላይ ብዛት ከአምስት መብለጥ የለባቸውም፡፡
- በእያንዳንዱ ድንጋጌ <ሀ>፣<ለ>፣<ሐ>፣<መ>፣<ሠ> ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ እንኳን ተሟልቶ ቢገኝ አንድ የቅጣት ማቅለያ እንደተሟላ ተደርጎ

# ...የቀጠለ

- በእያንዳንዱ ድንጋጌ <ሀ>፣<ለ>፣<ሐ>፣<መ>፣<ሠ> ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሲቀል የሚደርስበት የቅጣት እርከን ውስጥ ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ከዝቅተኛው እስከ ጣሪያው ባለው ውስጥ ቅጣቱ የሚወድቅበትን ይወስናል፡፡
- በቀላል እና በፅኑ እስራት ለሚያስቀጡ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን አንድ እርከን ወደታች ይቀንሳል፡፡
- ስለሆነም በቅጣት ማቅለያዎቹ ቁጥር ልክ የቅጣት እርከኑም እንደዚሁ ይቀንሳል፡፡
- ይሁንና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 ከተደነገገው ዝቅተኛ ወለል በታች ሊወርድ አይችልም፡፡
- በቀላል እና ፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራራቢ ሆነው የሚደመሩ በሆነ ጊዜ በቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የሚቀንሰውን እርከን መጠን ለመወሠን የቀላል እስራት ቅጣት በሕጉ አግባብ ወደ ፅኑ እስራት ተቀይሮ ቅጣቶቹ ተደምረው የሚመጣው ውጤት የቅጣት መነሻ ተደርጎ ይወሠዳል፡፡

## ልዩ የቅጣት ማቅለያዎች

- በወንጀል ሕግ ቅጣትን በመሰለው እንዲያቀል በፈቀደ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት ሳይወሰን ቅጣቱን በማቅለል ይወስናል፡፡

## በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 መሠረት የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች በሚኖሩ ጊዜ ስለሚሰላበት ሁኔታ

- ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 መሠረት የቅጣቱን ማቅለያ ወይም ማክበጃ ምክንያቶች የሚጠቀም በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ ጠቅላላ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ እንደሚኖረው አሰራር ቅጣቱን በማክበድ ወይም በማቅለል ይወስናል፡፡

## የቅጣት አሰላል ሥነ ሥርዓት ቅደም ተከተል

- የወንጀል ደረጃ የወጣላቸውን የወንጀል አይነቶች በተመለከተ፣
  - የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የወንጀሉን ደረጃ ይወስናል፡፡
  - የወንጀሉ ደረጃ የሚወድቅበትን የቅጣት እርከን በቅጣት ሠንጠረዥ ላይ ይለያል፡፡
  - ድንጋጌው ቀላልና ፅኑ እስራትን በአማራጭነት ባስቀመጠ ጊዜ ፍ/ቤቱ ወንጀሉ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ይወስናል፡፡
  - በእርከኑ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ባለው ፍቅድ ስልጣን **(range)** ውስጥ መነሻ ቅጣት ይወስናል፡፡
  - ይሁንና ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸው የቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያ ምክንያቶች ካሉ በዚህ ድንጋጌ መሰረት መነሻ ቅጣቱን መወሰን ሳያስፈልግ ቅጣቱን ያከበዳል ወይም ያቀላል፡፡

# ...የቀጠለ

- ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ካሉ በዚህ መመሪያ መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ቅጣቱ የሚደርስበትን እርከን ይወስናል፡፡
- ፍ/ቤቱ በተቀበለቻቸው ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ/ማቅለያ ምክንያቶች መሠረት እርከኑን ይወስናል፡፡
- ሆኖም ክርክር የተነሳባቸው የቅጣት ማክበጃ/ማቅለያ ምክንያቶችን በማስረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቂ ጊዜ ሰጥቶ ሊያጣራ ይችላል፡፡
- የሚጣለው የእስራት ቅጣት ከስድስት ወር ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሠንጠረዥ መሠረት በግዴታ ስራ እንዲለወጥ ሊወስን ይችላል፡፡
- በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣትን ወደ መቀጮ መቀየር እንደሚቻል በሕግ በተደነገገው መሠረት ወደ መቀጮ ሲቀየርም በዚህ መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

# ...የቀጠለ

- የወንጀል ደረጃ ያልወጣላቸውን የወንጀል አይነቶች በተመለከተ፣

➢ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በድንጋጌው በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት ሊያስቀጣ እንደሚችል የተደነገገ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን በቅድሚያ ይለያል፡፡

➢ የወንጀሉ ከባድነትን በተመለከተ <ቀላል> ወይም <መካከለኛ> ወይም <ከባድ> በማለት ይለያል፡፡

➢ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት መነሻ ቅጣቱን በመወሰን፣ በቅጣት እርከን ሠንጠረዥ የሚያርፍበትን የቅጣት እርከን ወይም የመቀጮ እርከን ይለያል፡፡

➢ ከዚህ በመቀጠል በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት ስሌቱን በመስራት ቅጣቱን ይወስናል፡፡

- የወንጀል ደረጃ የወጣላቸው እና ያልወጣላቸው የወንጀል ዓይነቶች ተደራረበው ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንጀል በዚህ መመሪያ መሠረት የመነሻ ቅጣት ከተወሰነ በኋላ የሁለቱ ድምር የመነሻ ቅጣት ሆኖ ይወሰዳል፡፡

## ከመመሪያው ውጭ ቅጣት ሊወሰን  የሚችለበት ስርዓት

- ዳኞች ከመመሪያው ወጥተው የሚወስኑት ፍትህ እንዳይጓደል ሲሆን ዉጤቱም መመሪያውን ለማሻሻል ወይም አግባብ ባልሆነ መንገድ ከመመሪያው ወጥተው ከወሰኑም በቀጣይ በተመሣሣይ መንገድ እንዳይወሰን የሚያግዝ አሰራር ለመቀየስ የሚጠቅም ነው፡፡
- ስለዚህ ይህ ድንጋጌ ለቅጣት አወሳሰን ሥራ መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው ነው፡፡
- በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባህርይው በዚህ መመሪያ ደረጃ በወጣላቸው ሊወከል የማይችል ሆኖ ባገኘው ጊዜ ወይም በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት አላማ እና ግብ የማያሳካ  ነው ብሎ ካመነ፣ የዚህን የቅጣት መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስን ይችላል፡፡

# ...የቀጠለ

- ዳኞች ከመመሪያው ውጪ ቅጣትን ከወሠኑ መረጃው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ግልፅ ትዕዛዝ ሊሰጡ ይገባል፡፡
- የክልል ፍ/ቤቶችን በተመለከተ የውሳኔ ግልባጭ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በኩል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲላክ ማድረግ አለባቸው፡፡
- ፍርድ ቤቱ በዚህ መሰረት መመሪያው ከሚያስቀምጠው በተለየ እርከን ላይ እንዲያርፍ በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ ግልባጭ ውሳኔ ከተሰጠበት ጀምሮ በ60 (በስልሳ) ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

## የንብረት ግምት መወሰንን በተመለከተ

- ወንጀሉ የተፈጸመው በውጭ ሀገር መገበያያ ገንዘብ ላይ ከሆነ፣ የገንዘቡ ምንዛሪ መጠን ወንጀሉ ሲፈፀም በነበረው የምንዛሬ ተመን መሠረት ይሆናል፡፡
- በወንጀሉ የተወሰደው ንብረት በሚሆንበት ጊዜ የንብረቱን ግምት በተመለከተ ተከሳሹ ክርክር ካቀረበ እና የተከሳሹ ክርክር ተቀባይነት ቢያገኝ የቅጣት እርከኑን የሚቀየር ከሆነ እና በፍርድ ቤቱ እምነት በዐቃቤ ህግ የቀረበው ግምት ምክንያታዊ ያልሆነ ነው ብሎ ሲያምን የራሱን ግምት በማስቀመጥ ወይም በባለሙያ በማስገመት የወንጀል ደረጃውንና የቅጣት እርከኑን ይወስናል፡፡
- ተከራካሪ ወገኖች በግምቱ ላይ ክርክር ባያነሱም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ የንብረቱን ግምት ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሊያጣራ ይችላል፡፡
- ከንብረቱ ልዩ ባህሪ የተነሳ ግምቱን በገንዘብ መተመን ያልተቻለ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በራሱ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ቅጣቱን ሊወስን ይችላል፡፡

## ስለቅጣት አስተያየት አቀራረብ

- አቃቤ ሕጎችም ሆኑ ጥፋተኞች ወይም ጠበቆቻቸው የቅጣት ውሳኔ አስተያየት በሚያቀርቡበት ጊዜ በዚህ መመሪያ መሰረት መሆን አለበት፡፡
- ፍ/ቤቶችም በመመሪያው መሠረት የቅጣት አስተያየቶች መቅረባቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
- በጠበቃ ለማይወከሉ ተከሳሾች በመመሪያው መሰረት የቅጣት አስተያየት ማቅረብ እንዳለባቸው ፍ/ቤቱ ሊገልጽላቸው ይችላል፡፡

ተፈፀመ።።

አመሰግናለሁ!!